# አዋልድና ራዕይ - ነክ ጽሑፎች

## አዋልድ

«አዋልድ» የተባለው ስም በላቲኑ ቮልጌት ውስጥ የሚገኙት፥ ነገር ግን በዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የማይገኙት መጻሕፍት የሚጠሩበት ስም ነው። እነዚህ መጻሕፍት በቮልጌት ውስጥ ሊገኙ የቻሉበት ምክንያት ከዕዝራ ሱቱኤል በስተቀር ሁሉም በላቲን በተተረጎመው የግሪኩ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ተጠቃልለው በመገኘታቸው ነው። በዘልማድ እንደተነገረው፥ በእስክንድርያ ይኖሩ የነበሩ ተናጋሪ አይሁዶች እነዚህ መጻሕፍት በአንድነት እንዲጠረዙ አድርገዋል፤ በተጨማሪም በግሪክ ብሉይ ኪዳን ትጠቀም የነበረችውም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ተቀብላቸዋለች። መጻሕፍት በእስራኤል አገር በዕብራይስጥ ወይም በአራም ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው፤ በእስራኤልና በተበተኑት አይሁዶች የተወደዱ ቢሆኑም በሁሉም የተሰጣቸው ሥፍራ ግን ከቤተ ክርስቲያን ጥራዝ የተለየ ይመስላል። በዚህ መሠረት አንድ ምሁር «አዋልድ» ለሚለው ተስማሚ የሆነ ዓይነተኛ ቃል «ውጪያዊ» መጻሕፍት የሚለው ነው በማለት ሐሳቡን ሰንዝሯል።

ይህ መልካም የሆነ አቻ ቃል ቢሆንም «አፓክሪፎስ» ለሚለው የግሪክ ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ አይደለም። የዚህ የግሪክ ቃል ትርጉም «የተደበቀ» ማለት ሲሆን ከተራ ምዕመናን ዐይን ተሰውረው ለተቀመጡትና እንዲያነቡ መብት በተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ለሚነበቡት መጻሕፍት መጠሪያ ነበር። የቃሉ ትርጉም የመጻሕፍትን ጥቅም ዝቅ የሚያደርግ ሳይሆን ይህንን ስም ያገኘ መጻሕፍት ልዩ ደረጃ ያላቸው መሆኑን ያሳያል። «ድብቅ» የሚለውን ልዩ ስም ያተረፉት መጻሕፍት በ2ኛው መቶ ዓክልበና በ1ኛው መቶ ዓ.ም. መካከል ትንቢት ተናጋሪዎች አይሁድ የተጻፉ ናቸው። የጥንት የእስራኤል ጀግኖችንና ነቢያትን ስም ተጠቅመው በተዘዋዋሪ መንገድ ለአንባቢያን ሲያቀርቡ ጥንት ተጽፈው በቅርቡ የተገኙ ናቸው በማለት ነበረ፤ ይሁን እንጂ ለጉባዔ ሳይሆን ለጥቂት ሰዎች ብቻ የተፈቀዱ ነበሩ ይባላል። ለምሳሌ ዕዝራ 94ቱን መጻሕፍት ለ5 ጸሐፊዎች እንዴት እንደጻፈ ዕዚ.ሱቱ.13፡42-45 ይገልጻል። ከነዚህ መጻሕፍት መካከል 24ቱ የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች ሲሆኑ 70ዎቹ «የዕውቀት ምስጢር፥ የጥበብ ምስጢር እና እንደ ፈሳሽ ውኃም ያለ ዕውቀት ያላቸው አለቆች» የጻፉዋቸው ናቸው፤ ዕዚ.ሱቱ.13፡46፥ 47። በአቆጣጠሩ የመጨረሻዎቹ 12ቱ የነቢያት መጻሕፍት እንደ አንድ መጽሐፍ ተቆጥረዋል።

ይህ ጥቅስ የሚያሳየን እነዚህ መጻሕፍት ከብሉይ ኪዳን «በላይ» ዋጋ እንደተሰጣቸው ብቻ ሳይሆን አዋልድ በኛ ጥራዝ ውስጥ ከሚገኙት የበለጠ በጣም በዛ ያለ መጻሕፍትን ማጠቃለሉን ነው። እነዚህም ከዕዝራ ሱቱኤል ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ራዕይ ነክ መጻሕፍት ነበሩ።

አንድ ምሁር «አዋልድ» የሚለውን ቃል ራዕይ ነክ ጽሑፎችን ለማመልከት የሚጠቀምበት ሲሆን እኛ «አዋልድ» ብለን የምንጠራቸውን ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ይላቸዋል። በ1ኛና በ2ኛ ሳሙኤል መቅድሙ ውስጥ የቀድሞዎቹ ጸሐፊዎች ከህነታዊ ወይም በቤተ ክርስቲያን ለመነበብ የሚስማሙ መጻሕፍት ብለው ይጠሯቸው የነበሩትንና እኛ ደግሞ በተለምዶ «አዋልዳዊ» የምንለው የእነዚህን መጻሕፍት መጠሪያ

ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት ጀሮም የተባለው ምሁር ነበር። ለመደምደም ያህል፣ በጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት ውስጥ አዋልድ ማለት ከቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ውጭ ሆነው ከአይሁድ ሃይማኖት ወይም ከክርስትና ጋር አንድ ዓይነት ግንኙነት ያላቸው መጻሕፍት ማለት ነው። ጥቂቶቹ ከተቀሩት ይልቅ በጣም ተወዳጅ ስለነበሩ በላቲኑ «ቮልጌት» ውስጥ ተጠቃልለው ቀርበዋል። ይሁንና በቀድሞው ጸሐፊዎች የቀረቡት ከፍተኛ ዋጋ ቢሰጣቸውም አብዛኞቹ የተጻፉት ደራሲዎቻቸው ባልሆኑ ሰዎች ስም በመሆኑ ከሌሎች የተለዩ ተደርገው ሊወሰዱ አይገባም። ከዚህ የተነሣ «አዋልድ» የሚለው ቃል በተለያዩ ምክንያቶች መብት ያገኙትን፣ ከቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ውጭ ያሉትን መጻሕፍት በሙሉ እንዲይዝ ቢደረግ መልካም ነው።

## የአዋልድ መጻሕፍት ዝርዝር

ቀጥሎ የቀረበው የአዋልድና ደራሲዎቻቸው ባልሆኑ ስሞች የተጻፉት መጻሕፍት አጭር ዝርዝር መግለጫ ነው።

## መደበኛ የአዋልድ መጻሕፍት

*መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ*:-በውስጡ የያዘው በቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ውስጥ ባለው በመጽሐፈ ዕዝራ ውስጥ የሚገኘውን ጽሑፍ ሲሆን በተጨማሪም 2ኛ ዜና 35፡1-36፡21ን ያካልበታል። እንዲሁም የነህምያን ስም ሳይጠቅስ በነህ.8 ውስጥ የሰፈረውን የዕዝራን የእሪትን ሕግ ታሪክ ይጨምርበታል። ከ2ኛ ዜና 35፡1-36፡21 የተቀዳው ክፍል ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ከተጠቀመችበት ትርጉም ትንሽ ለየት ያለ ነው፤ ምናልባትም ትርጉሙ በጣም ጥንታዊ ሳይሆን አይቀርም። በተጨማሪም ዳርዮስ ባዘጋጀው ግብዣ ላይ የተገኙት የሦስቱ የቤተ መንግሥት ባለሚሎች ታሪክ ይገኝበት ይሆናል፤ ከባለሚሎቹ አንዱ ዘሩባቤል ይባላል። እርሱም «ጽድቅ ደግ ናት፤ ከሁሉም ትበልጣለች» የሚለውን አባባል ያመነጨ ሰው ነው፤ ዕዝራ ካልዕ 4፡41።

*መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል*:- በዕዝራ አዕምሮ ውስጥ የተቀመጠ የ1ኛው መቶ ዓ.ም. ራዕይ ነክ ጽሑፍ ሲሆን ከአንዳንዶቹ አንጻር ሲታይ ከሌሎቹ ራዕይ ነክ ጽሑፎች ሁሉ ልብን የሚነካ ነው።

*መጽሐፈ ጦቢት*:- ጦቢት ጥበቃ ያልተደረገለትን ሬሳ ሲቀበር ያሳየው አዘኔታ በመጨረሻ ዘመኑ እንዴት ሽልማት እንዳሰጠውና ልጁ ጦቢያ እንዴት ሚስት ሊያገኝ እንደቻለ የሚናገር የፍቅር መጽሐፍ ነው፤ የተጻፈውም ምናልባት በ3ኛው መቶ ዓክልበ መጨረሻ ላይ ሳይሆን አይቀርም። አንዳንድ በዕብራይስጥና በአራም ቋንቋዎች የተጻፉ የዚህ መጽሐፍ ቅዳጆች በኩምራን ገዳም ተገኝተዋል።

*መጽሐፈ ዮዲት*:- ዮዲት ከተማዋን ከአሶራውያን ሠራዊት እንዴት እንዳዳነች የሚተርክ አጠር ያለ ከፍተኛ ልብ ወለድ ነው። የተገኘውም በመቃብያን ዘመን ማለት በ150 ዓክልበ ሳይሆን አይቀርም።

*የመጽሐፈ አስቴር ጭማሪዎች*:- ታሪኩ በተፈጸመበት ዘመን የተጠቀሱ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ውስጥ ለሚገኘው ለመጽሐፈ አስቴር ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ጸሎቶችና ትእዛዛት የመሳሰሉትን የያዙ ጽሑፎች ናቸው። መጽሐፉንም ሃይማኖታዊ ይዘት እንዲኖረው ያደርጉታል ተብለው የታሰቡ ነበሩ።

መጽሐፈ ጥበብ፡- ይህ ምንጊዜም ቢሆን በሁለቱ ኪዳኖች መካከል የነበረው ዘመን ከፍተኛ ውጤት ተደርጎ የሚታሰብ መጽሐፍ ነው። ይህ በእስክንድርያ ይኖሩ የነበሩ ግሪክ ተናጋሪ አይሁድ ጽሑፍ ሲሆን ግሩም የሆነ የአይሁድ የጥበብ ጽሑፎች ምሳሌ ነው። ይህ መጽሐፍ በተለይ በቅጣትና በጣኦት አምልኮ ከንቱነት ትምህርቶች ላይ ያተኩራል። የተጻፈበት ዘመን ከ 150 ዓክልበ - 40ዓ.ም. ባለው መካከል እንደሆነ በተለያየ ሁኔታ ተገልጿል። አብዛኛው ጊዜ «የኢያሱ ሲራክ ጥበብ» ተብሎ የሚጠራው መጽሐፈ ሲራክ ቀደም ብለን ከተመለከትነው ከመጽሐፈ ጥበብ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይሁን እንጂ መጽሐፉ በተግባር ላይ ከዋለበት ዘመንና ከጸሐፊው ኑሮ አንጻር ሲታይ ከመጽሐፈ ጥበብ ይልቅ ይሄኛው በመንፈሳዊ ይዘቱ በጣም ያነሰ ነው፤ የተጻፈውም በ180 ዓክልበ በዕብራይስጥ ሲሆን፥ በጸሐፊው የልጅ ልጅ ወደ ግሪክ የተተረጎመው በ132 ዓክልበ ነበር።

መጽሐፈ ባሮክና የኤርምያስ መልዕክት፡- ጣኦት አምልኮን በመቃወም የተጻፉ ጥምር ጽሑፎች ናቸው። የመጀመሪያው የተደረሰው በ3ኛው መቶ ዓክልበ፥ ሁለተኛው ደግሞ በ2ኛው መቶ ዓክልበ ሳይሆን አይቀርም። ከመጀመሪያው ጽሑፍ በኋላ የተጨመሩ ሦስት የመጽሐፈ ዳንኤል ተቀጥያዎች ይገኛሉ።

የሶስናን ታሪክ የሚያቀርበው የመጀመሪያው መጽሐፍ፡- ወጣቱ ዳንኤል ሞት ለተፈረደባት ቅን ሴት ፍትሕ የተሞላበት ፍርድ በመስጠት እንዴት ጥበቡን እንዳሳየ ይናገራል። በሁለተኛ ደረጃ ያሉት የአዛርያስ ጸሎትና የሦስቱ ደቂቃን መዝሙር መጻሕፍት የቀረቡት በእቶን እሳቱ ውስጥ እንደተነገሩ ተደርገው ነው።

ቤልና ዘንዶው የተሰኙት ሁለት የተለያዩ ታሪኮች ሲሆኑ፥ የሚተርኩትም ዳንኤል የቤልን ካህናት እንዴት አድርጎ ዋጋ እንዳሳጣቸውና ዘንዶው አምላክ መሆኑን የሚናገረውን ሐሳብ ከነዘንዶው እንዳጋለጠ ነው።

የምናሴ ጸሎት የተሰኘው ሦስተኛው መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ በዚህ ስም በተጠራው ንጉሥ ልብ ውስጥ የተቀመጠ የንሥሐ ጸሎት ሲሆን በሁለተኛ ዜና 33፡12-19 ላይ የተመረኮዘ ነው፤ የተጻፈውም በ2ኛው መቶ ዓክልበ ሳይሆን አይቀርም።

1ኛ መቃብያን ወይም መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ፡- አይሁድ በማታትያስ ልጆች መሪነት ከአንቲዮክስ ኤፒፋነስና ከተከታዮቹ ጋር ያደረጉትን ትግል የሚነግረን ዋናና የመጀመሪያ ታሪክ ነው። ጸሐፊው ይህንን ታሪክ የጻፈው በግምት ከ135-104 ዓክልበ በነበረው የዮሐንስ ሂርካኑስ ዘመን ሲሆን የአሰሞናውያን ወገን የነበር አንድ አርበኛ ሊጽፍ ከሚችለው አንጻር ሲታይ እጅግ ጎበዝ የታሪክ ሰው ነበር።

2ኛ መቃብያን ወይም መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ የሚያተኩረው በቀደመው መጽሐፍ ከፊል ዘመን ላይ ሲሆን በተለይም በይሁዳ መቃቢስ የጀግንነት ተግባር ላይ ነው፤ እንዲሁም ከመጀመሪያው ይልቅ ብዙ የተጋነኑ ታሪኮች የታከሉበት መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ከቀድሞ ፈሪሳውያን አመለካከት አንጻር የተጻፈ በመሆኑ አንቲዮክስ በገደላቸው ሰማዕታት የትንሣኤ ተስፋ ላይ ትኩረት ያደርጋል። በተጨማሪም በቤተ መቅደሱ ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል።

## ጸሐፊዎቻቸው ባልሆኑ ሰዎች ስም የተጻፉ መጻሕፍት

መጽሐፈ ሄኖክ ወይም 1ኛ ሄኖክ:- በዚህ ምድብ ውስጥ ከተመደቡት ጽሑፎች ሁሉ እጅግ በጣም ታዋቂነት ያተረፈ ራዕይ ነክ ጽሑፍ ነው። መጽሐፉ የተለያዩ ሰዎች የጽሑፎች ቅንብር ለመሆኑ አያጠራጥርም። ይሁን እንጂ መጽሐፉ በአንድ ዘመን የተገኘ ይሁን ወይም ቀስ በቀስ ተጠራቅሞ በሄኖክ ስም ከ200 ዓክልበ እስከ 1ኛው መቶ ዓ.ም. ድረስ የተጻፉ ለመሆናቸው የተረጋገጠ አይደለም። ከሚያቀርበው ትምህርት አንጻር ሲታይ የመጽሐፉ ዋና ጥቅም የሰው ልጅ በመባል ከሰማይ በሚመጣው መሢሕ ላይ በማተኮር የሰጠው አስተያየት ነው። መጽሐፈ ሄኖክ ምዕ.37:71 በአራም ቋንቋ የተጻፉ የመጽሐፈ ሄኖክ ቅዳጆች ከነዚህ ምዕራፎች በስተቀር በኩምራን ገዳም ውስጥ ተገኝተዋል።

በይዘቱ አሪት ዘፍጥረትን የሚመስለው መጽሐፈ ኩፋሌ የተባለው መጽሐፍ ሲጻፍ ሦስት ዓላማ ነበሩት፤ ይኸውም:- የኦሪት ሕግ መከበር የጀመረው ከገነት እንደነበር ለማስረዳት፥ ወራት በጨረቃ ሳይሆን በፀሐይ እንቅስቃሴ እንዲቆጠሩ ለማዘዝና ታሪክ በኢዩቤልዩ ዘመናት ማለት በ49 ዓመታት ወይም በሰባት የሱባኤ ዓመታት የተከፈለ መሆኑን ለመግለጥ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ተጽፏል ተብሎ የሚነገረው በ100 ዓክልበ ነው። የዚህ መጽሐፍ የዕብራይስጥ ቅጂ ቅዳጆች በኩምራን ገዳም ተገኝተዋል።

የ12 አበው ኪዳኖች የተሰኘው ጽሑፍ የተጻፈው ከመጽሐፈ ኩፋሌ ጋር በተመሳሳይ ዘመን ሳይሆን አይቀርም። መጽሐፉ 12ቱ የያዕቆብ ልጆች ለሞት ሲቃረቡ እያንዳንዳቸው የሰጧቸውን የመጨረሻ ምክሮችና ትንቢቶችን ያቀርባል። የመጽሐፉ የግሪክ ቅጂ በአንድ ክርስቲያን ታርሞ የተዘጋጀ ቢሆንም ታርመው በአረምና በዕብራይስጥ ቋንቋዎች የተጻፉ ቅጂዎቹም በኩምራን ገዳም ተገኝተዋል።

የሲቢሊን ራዕዮች የተሰኙት ጽሑፎች በአሕዛብ መካከል የአይሁድን አስተሳሰብ ለማስፋፋት ይመች ዘንድ የአራሚ የጥንቆላ ነቢያቶችን የመገለጥ ዘዴ በመቅሰም የተጻፉ የአይሁድ መጻሕፍት ናቸው፤ የተገኙትም ከ2ኛው መቶ ዓክልበ ወዲህ ባሉት ዘመናት ውስጥ ነው።

የሙሴ ንጥቀት የተባለው ጽሑፍ የታየው ምናልባት ጌታችን በኖረበት ዘመን ሳይሆን አይቀርም። ይህ መጽሐፍ በትንቢት ሽፋን ቀርቦ ከሙሴ አንሥቶ እስከመጨረሻ ማለትም ጸሐፊው እስከኖረበት ዘመን ድረስ ያለውን የዓለም ታሪክ ለማቅረብ ሞክሯል።

የሄኖክ የምስጢራት መጽሐፍ ወይም 2ኛ ሄኖክ:- ከመጽሐፈ ሄኖክ የሚቀጥልና በ1ኛው መቶ ዓክልበ አጋማሽ ላይ የተጻፈ ሳይሆን አይቀርም። አንዳንዶች ግን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ብዙ መቶ ዓመታት ቆይቶ እንደተጻፈ ይገምታሉ። ይህ መጽሐፍ ስለ ሰባቱ ሰማያት የተብራሩ መግለጫዎችን የሚሰጥና የ1000 ዘመን የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንደሚሆን ተስፋ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው።

የሶርያውያን የባሮክ ራዕይ ነክ ጽሑፍ ወይም 2ኛ ባሮክ የተሰኘው ጽሑፍ ከሞላ ጎደል በመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ላይ የተመረኮዘና የተለያዩ ሰዎች የጻፉት ቅንብር ሲሆን ትንቢተ ኤርምያስን የጻፈ ጸሐፊ ጽፎታል ይባላል። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በ1ኛው መቶ ዓ.ም. ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ ነው።

የግሪኩ የባሮክ ራዕይ ወይም 3ኛ ባሮክ የተባለው ጽሑፍ ቀደም ብለን ከጠቀስነው የባሮክ መጽሐፍ ጋር የሚዛመድ ሲሆን ጸሐፊው ግን አንድ አይደለም፤ የተጻፈውም ከርሱ በኋላ ሳይሆን አይቀርም።

መዝሙረ ሰሎሞን የተባለው መጽሐፍ በውስጡ አሥራ ስምንት መዝሙሮችን ያቀፈ በሰሎሞን ስም የተጻፈ መጽሐፍ ነው፤ ይሁን እንጂ የተጻፈው በፈሪሳዊ ወይም የፈሪሳውያን አመለካከት ባለው ሰው ነው። እነዚህ መዝሙሮች በቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ውስጥ በሚገኘው በመዝሙረ ዳዊት የአጻጻፍ ስልት የተጻፉ ሲሆን ሮማውያን ይሁዳን ድል ካደረጓት በኋላ በ1ኛ መቶ ዓ.ም. ሁለተኛ አጋማሽ ውስጥ የተጻፉ ናቸው። በተጨማሪም ሐስሞናውያንን የሚያወግዙና ከዳዊት ዘር የሚወለደውን መሢሕ መምጣት የሚጠባበቁ ነበሩ።

3ኛ መቃብያን ወይም መጽሐፈ መቃብያን ሳልሳዊ ከ 222-205 ዓክልበ በነበረው በፕቶለሚ ፊሎፓተር ዘመነ መንግሥት አይሁድን ለመፍጀት ስለተደረገው ሙከራና በእግዚአብሔር ቅን ፍርድ ሐሴት ስላደረገው ቅዱስ ሕዝብ ይናገራል።

4ኛ መቃብያን ትክክለኛ አስተሳሰብ ምንጊዜም ድል ያደርጋል የሚለውን የጸሐፊው መርሆ ለማስረዳት የመቃብያንን ሰማዕታት ታሪኮች በመጠቀም የተጻፈ ፍልስፍና ነክ ጽሑፍ ነው።

የአርስቲአል መልዕክት የዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክ ተተርጉሟል ተብሎ ይታመንበት የነበረውን የሰዎችን እምነት የሚገልጽ ነው። ኢሳይያስ ሰማዕታት የተባለው ጽሑፍ ርዕሱ እንደሚጠቁመን የኢሳይያስን በመጋዝ ለሁለት መሰንጠቅ ይነግረናል።

አንድ ምሁር መጽሐፉ የተጻፈው በ1ኛ መቶ ዓ.ም እንደሆነ ቢናገርም እንኳ ይህ መጽሐፍ የተገኘው የኢሳይያስ ዕርገት ከተባለው በኋለኛው ዘመን በክርስቲያኖች ከተጻፈው መጽሐፍ ሳይሆን አይቀርም። ይሁንና ይህ ጽሑፍ ከኩምራኑ ጽሑፍ ጋር ተዛምዶ ከቀድሞ የአይሁድ ታሪክ ጋር የተዋሐደ ሊሆን ይችላል።

የአዳምና ሔዋን መጻሕፍት ስለ ትውልድ አባቶች አኗኗር በርካታ «መረጃዎችን» የሚያቀርቡና በ1ኛው መቶ ዓ.ም ላይ ብቅ ያሉ ጽሑፎች ናቸው።

የአበው ንግግሮች የተባለው ጽሑፍ የታወቁ የአሪት ሕግ መምህራንን ንግግሮች የያዘ ስብስብ ጽሑፍ ሲሆን ከ3ኛው ዓክልበ እስከ 3ኛው ዓ.ም. ድረስ ያለውን ዘመን የሚያጠቃልል ነው።

የአኪአክሮስ ታሪክ የተባለው ጽሑፍ በርዕሱ ላይ የተጠቀሰውን የዚህ የብልሃተኛ ሰው ጥበብ የሚናገር የ5ኛው መቶ ዓክልበ አፈ ታሪክ ሲሆን በዘመኑ ተወዳጅ የነበረ ጽሑፍ ነው፤ ጦቢት 14፡10 ተመልከቱ።

የአብርሃም ራዕይና የአብርሃም ኪዳን ከ1ኛው መቶ ዓ.ም የተገኙ ክርስቲያናዊ ለውጦች የተደረገባቸው የአይሁድ ጽሑፎች ናቸው።

የነቢያት ኑሮ የተባለው ጽሑፍ ርዕስ እንደሚጠቁመው የሚያወራው ስለ ነቢያት ነው፤ የተገኘውም ቀደም ብሎ ከተጠቀሱት ሁለት ጽሑፎች ጋር በተመሳሳይ ዘመን ሲሆን ይኼኛው እንደነርሱ የተስፋፋ ጽሑፍ ነው።

የኢዮብ ኪዳን የተባለው ጽሑፍ እምብዛም ትኩረት ያልተሰጠው ጽሑፍ ሲሆን አንዳንዶች በ1ኛ መቶ ዓክልበ እንደተጻፈ ገምተዋል።

የሳዶቃውያን ሰነዶች በመባል የሚታወቁት በቀድሞው ካይሮ ምኩራብ ውስጥ የተገኙ ተሟልተው ያልተጻፉና ከሞላ ጎደል እርስ በርስ የሚደጋገፉ ሲሆን በመካከለኛው ዘመን መጀመሪያ ገደማ የተጻፉ ሁለት የዕብራይስጥ ብራናዎች በአሁኑ ወቅት የኩምራን ገዳም ጽሑፍ አካል መሆናቸው ተደርሶበታል። ከዚህም በላይ በኩምራን ዋሻዎች ውስጥ የተገኙት ሌሎች ቅዳጆች ሰነዶች ከ1ኛው መቶ ዓክልበ መጀመሪያ አንስቶ የተጻፉ መሆናቸውን ያመለክታሉ።

እ.ኤ.አ. ከ1947 ወዲህ ባሉት ዓመታት ውስጥ ከጨው ባሕር በስተሰሜን ምዕራብ በሚገኙት በ11 የኩምራን ዋሻዎች ውስጥ በአመዛኙ የተቀዳደዱ 500 የሚያህሉ ሰነዶች መገኘት የዘመኑን የአይሁድ ጽሑፍ ክምችት በጣም ከፍ አድርጎታል። እነዚህ ሰነዶች ከ130 ዓክልበ - 70 ዓ.ም ዋና መምሪያው በኩምራን የነበረውን ተገንጣይ ኅብረተሰብ መጻሕፍት ቤት በከፊል ያደራጁ ጽሑፎች ይመስላሉ። ይህ ኅብረተሰብ በ1ኛው መቶ ዓ.ም. በአይሁድ ጸሐፊዎች ከተገለጸው የባሕታውያን ቡድን ጋር በጥቂት የሚመሳሰል ሲሆን፡ የዚህ ኅብረተሰብ ልዩ ትምህርትም ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የተረፍነው እኛ ብቻ ነን የሚልና በመጨረሻ ነገሮች ላይ ባለው ጽኑ እምነት እንዲሁም ግልጽ በሆነውና ንቃት ባለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንታኔ ላይ ያተኮረ ነበር። የኩምራን ጽሑፎች በሙሉ በአዋልዳዊና ጸሐፊዎቻቸው ባልሆኑ ሰዎች ስም በተጻፉት ጽሑፎች ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉ አይደሉም። በተጨማሪም የኩምራን ገዳም ጽሑፎች የመጽሐፍ ቅዱስ ግልባጮችና ማብራሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ አንዳንዶቹ የገዳሙን ኑሮ፥ እምነቶችና አምልኮ የያዙ ናቸው።

ከፍ ተብሎ ከተጠቀሱትና በትርጉም ብቻ ከሚታወቁት መጻሕፍት መካከል አንዳንዶቹ በኩምራን ጽሑፎች አማካይነት በመጀመሪያ የተጻፉበት ቋንቋ ተደርሶበታል። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን ጥራዝ ውስጥም ሆነ በአዋልድ መጻሕፍት ውስጥ ሥፍራ ያላገኘው የትንቢተ ዳንኤል ጭማሪ ይገኝባቸዋል። የባቢሎን ንጉሥ በቴማን ከተማ ለሰባት ዓመታት እንዴት በቁስል እንደተሠቃየና ኃጢያቱን ሲናዘዝ ከአንድ አይሁዳዊ ምርኮኛ እንዴት እርዳታ እንዳገኘ የሚናገረው የናቢነዶስ ጸሎት የተባለው የአራምኛ መጽሐፍም በውስጡ ይገኝበታል። በዘፍጥረት፥ አዋልድ የተባለው የአራምኛ ጽሑፍ ደግሞ የቀድመ አባቶችን ታሪኮች በልበወለድ መልክ አስፋፍቶ የያዘ ጽሑፍ ነው። የተቀሩት ጽሑፎች፡- የሙሴ ንግግሮች፥ መዝሙረ ኢያሱ፥ የአራም ራዕይ፥ መጽሐፈ ምስጢራትና የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ራዕይ በሚሉ ርዕሶች ሥር የቀረቡ ናቸው። የመጽሐፈ ምስጢራት ቅጂዎች ብዙ ስለሆኑ በጣም ተወዳጅ ነበሩ ማለት ያሰኛል። እነዚህ ጽሑፎች ሁሉ ታትመው ቢወጡ በአዲስ ኪዳን አመጣጥ መሠረታዊ ነጥቦች ባለን ዕውቀታችን ላይ ተጨማሪ በመሆን ትልቅ ድርሻ ሊያበረክቱ ይችላሉ።

# የአዋልድ ጽሑፎች ትምህርት

## ስለ እግዚአብሔር የተሰጠ ትምህርት

እነዚህ ጽሑፎች በብሉይ ኪዳን ተገልጦ የነበረውን እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ፍጥረታት ጋር የመሠረተውን ግንኙነት ሰርዘው እግዚአብሔር ከሰው የራቀና ግንኙነት የሌለው እንደሆነ አድርገው አጋንነው ያስተምራሉ። በተከታታይም የክርስቶስ መወለጃ ዘመን እየተቃረበ ሲመጣ ይህ ዝንባሌ እየተጋነነ ሄዷል። እነዚህ ጽሑፎች የእግዚአብሔርን ስም መጥቀስ ስለማይፈልጉ በተዘዋዋሪ መንገድ ይገልጹታል። በ1ኛ

መቃብያን ውስጥ አንድም ጊዜ እንኳ የእግዚአብሔር ስም በቀጥታ አልተጠቀሰም። ይሁን እንጂ ይበልጡን ጊዜ ሕልውናውን ማውሳት ሲፈልግ ሰማይ ብሎ ጠቅሶታል። ለምሳሌ «የውጊያ ድል የሚገኘው በሠራዊት ብዛት ሳይሆን ከሰማይ በሚመጣ ብርታት ነው» የሚለውን መመልከት ይበቃናል፤ 1ኛ መቃብ. 3፡19። አይሁዳዊው ጸሐፊ፥ ማቴዎስ በወንጌሉ ውስጥ እንደሌሎቹ ወንጌሎች «የእግዚአብሔር መንግሥት» በማለት ፈንታ «መንግሥተ ሰማያት ብሎ የተጠቀመውን ቃል ከዚህ ዝንባሌ ጋር ልናወዳድረው እንችላለን። የአይሁድ መምህራን እግዚአብሔርን ዘወትር የሚጠቅሱት «ቅዱሱ፥ የተባረከው» በሚል ሁኔታ ነበረ፤ ለምሳሌ «በነገሥታት ንጉሥ፥ በቅዱሱ፥ በተባረከው ፊት እውነተኛ ታሪካችሁንና ያደረጋችሁትን ትናገራላችሁ» የአበው ንግ. 4፡29። ተመሳሳይ በሆነ ምክንያት እግዚአብሔርን በዓለም ጉዳዮች ውስጥ ያለውን ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ መሆኑን ለማስቀረት ሲባል ስለ መላእክት ባቀረበው ትምህርት በዚህ ዘመን በጣም ተጋንኖ ይገኛል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር የእስራኤልን ውጊያዎች የሚዋጋ «ጦረኛ» ነበር። በ2ኛ መቃብያን ውስጥ እንደተገለጠው ለእስራኤል የሚዋጉት መላእክት እንደሆኑ ተደርጎ ሲሆን የእግዚአብሔርን ስም ግን አይጠቅስም። የኩምራን የውጊያ ደንብ በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ የብርሃን ልጆች ብለው ራሳቸውን ከሚጠሩት ከገዳሙ ነዋሪዎች ጎን በመሠለፍ ጦርነት የሚያካሂዱት ቅዱሳን መላእክት ናቸው። በ1ኛ መቃብያን ውስጥ ዝንባሌው እየጎላ ስለሄደ እግዚአብሔርም ሆነ መላእክት አይዋጉም፤ ሆኖም ይሁዳ የተባለው ግሩም የጦር አዝማች ሰው ድል ያስገኛል። እዚህ ላይ ያለው አስተሳሰብ እንደሚያሳየው እግዚአብሔር በዚህ ሥርዓት ጉዳዮች ውስጥ በቀጥታ ጣልቃ መግባቱ ይህን ያህል አስፈላጊ አይደለም የሚል ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከፍጥረት ጋር ያለው ቀጥተኛ ግንኙነት በአእላፋት መላእክት ተተክቷል። ከነዚህም መላእክት መካከል ጥቂቶቹ መብረቅን፥ የተቀሩት ሌሎቹ ደግሞ በረዶን፥ ዝናብን፥ ደመናን፥ ጨለማን፥ ሙቀትንና ውርጭን ወዘተ እንዲቆጣጠሩ ተሹመዋል። በሌላ አንጻር ደግሞ ለአጋንንት ትምህርት ተጨማሪ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን ለዚህም ሌሎች ምክንያቶች ቀርበዋል።

ለእግዚአብሔር ከተሰጠው ከዚህ አመለካከት ጋር እርሱ ከሁሉ በላይ ስለ መሆኑ የተሰጠው አስተሳሰብ እጅግ ከፍ ያለ ነበር። የመጨረሻው መገለጥ በቅድሚያ የታየ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ ሰዓቱ እንኳ ሳይቀር የተወሰነ ነው። በዚህ አስቀድሞ በመወሰን ሂደት ውስጥ ግለሰቦችም ተካፋዮች ሲሆኑ ይህም ነጻነታቸውን እንደጠበቀ ሆኖ ነው። የመዝሙረ ሰሎሞን ጸሐፊ እግዚአብሔር በሰው ላይ ፍጹም የበላይ መሆኑን ያምናል። ይሁን እንጂ «ሥራችን በእኛ ምርጫ የሚደረግ ነው፤ ቅን ወይም ጠማማ የማድረግ ኃይል በእጃችን ውስጥ ነው» 9፡7 በማለት ተናግሯል። እንዲሁም የእግዚአብሔር ከሰው ርቆ መኖር ከሰዎች ጋር ያለውን ዝምድና ጨርሶ አያስቀርም። እንዲያውም አባትነቱ በይበልጥ እየታወቀ መጥቷል። «በሰማይ ያለው አባታችሁ» የሚለው ሐረግ በአበው ንግግሮች 5፡23 ውስጥ ይገኛል። በተጨማሪ «እግዚአብሔር በልጆቹ ሐሴት ያደርጋልና ለዘላለምም በምርጦቹ እጅግ ይደሰታል» የሌዊ ኪዳን 18፡13፤ 4፡2፤ የሲሊቢን ራዕዮች 3፡702፤ 3ኛ መቃብ.6፡28ና የአበው ንግ.3፡19 አወዳድሩ።

## የአሪት ሕግ

በአዋልድ መጽሐፈ ትምህርት ውስጥ የኦሪት ሕግ ዘላቂና ለሰውም ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ተጠቅሷል። በመጽሐፈ ኩፋሌ ውስጥ የጥንት ጻድቃን ሰዎች በሙሉና የሰማይ

መላእክትም ጭምር የኦሪትን ሕግ ማክበራቸው ተነግሯል። ሙሴ በሲና ተራራ የፈጸመው ድርጊት ዳግም አወጀው እንጂ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታወቅ አላደረገውም። የኦሪት ሕግ የእግዚአብሔር መገለጥ አጠቃላይ ድምር ነው። በአብዛኛው አይሁድ ዘንድ ኦሪት ከሙሴ ጀምሮ በነቢያትና በታላላቅ የምኩራብ ሰዎች እንደተሰጠ የሚነገርለትን የአበውን ትውፊት ያጠቃልላል። ይህ ትውፊት በጽሑፍ የሰፈረው ከ200 ዓ.ም ወዲህ ነበር። ሚሽና ተብለው የሚጠሩት ብዙ ትላልቅ መጻሕፍት ትውፊትን ዘርዝረው ያብራራሉ፤ ገማራ የሚባሉት በርካታ መጻሕፍት ደግሞ ተጨማሪ ማብራሪያዎችና ትርጉሞች ያቀርባሉ። ሁለቱ ተጣምረው የኢየሩሳሌምና የባቢሎናውያን የተሰኙ ሁለት ስብስቦች ያሉትን «ታልሙድ»ን ፈጥረዋል። ጌታችን ለዚህ የትውፊት ስብስብ ያለው አቋም ምን ዓይነት እንደሆነ በሚገባ የታወቀ ቢሆንም ለአብዛኞቹ ወግ አጥባቂ አይሁድ ግን ይህንን ትውፊት ማክበር የሕይወታቸው ደም ሥር ነበር። የኦሪት ሕግ መምህራንና የተለያዩትን የራዕይ አዋልድ መጻሕፍት የደረሱ ሰዎች አንድ ሰው በሚመጣው ዓለም ሕይወት የማግኘት ተስፋ ያለው በታልሙድ መጻሕፍት ውስጥ ተዘርዝረው የሚገኙትን ሕግጋት ሲታዘዝ መሆኑን በማስተማር ይስማማሉ።

## ጥበብ

የግሪክ አስተሳሰብ በአይሁድ እምነት ውስጥ ራሱን እያሳወቀ በሄደ መጠን በምሳሌ 8፡22-31 ውስጥ የቀረቡት የጥበብ ባሕርያት በይበልጥ መታሰብ ጀመሩ። በመጽሐፈ ጥበብ ውስጥ ረጅምና ውብ የሆነ የጥበብ መግለጫ ይገኛል። ይኸውም «የእግዚአብሔር ኃይል እስትንፋስና የኃያሉ አምላክ ክብር ንጹህ ምንጭ ናት... ዘላለማዊው ብርሃን ነፀብራቅ እንከን የማይወጣላት የእግዚአብሔር ሥራ መስተዋትና የቸርነቱ አምሳል ናት» ይላል፥ መጽ.ጥበ.7፡22-8፡1። ነፀብራቅ ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል በዕብ. 1፡3 ደግሞ ይገኛል። በመጽሐፈ ጥበብና በመጽሐፈ ሲራክ በሁለቱም ውስጥ የጥበብ ተግባራዊ ምሳሌዎቹ ቀርበዋል።

እንዲሁም «የእግዚአብሔር ቃል» ለሚለው ፅንሰ ሐሳብ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶታል። የእግዚአብሔር ቃል ተግባር በጥበብ 18፡15-16 ውስጥ «አሸናፊ አርበኛና ሁሉን የሚችል ተጋዳይ የሚሆን ቃልህ ያቺን ሌሊት ተበቅሏታልና ያለማዳላት ያጠፏቸው ዘንድ ትዕዛዝህ የተሳለ ሰይፍን ታጥቆ ከሰማይ ወርዶ መንግሥት ባላቸው በግብፃውያን መካከል በቆመ ጊዜ ደዌያቸው ሁሉ ሞትን ተሞላ፤ ከሰማይ ወርዶ ተጫናቸው ከምድርም አጠፋቸው» ተብሎ በሚያስገርም ሁኔታ ተገልጿል። ይህ ጥቅስ የሚጠቁመው የግብፅን የበኩር ልጆች መገደል ነው። በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በምዕ.9፡1-2 ውስጥ « ... ያባቴ ፈጣሪ የቸርነት ባለቤት፥ በቃልህ ዓለሙን ሁሉ የፈጠርክ ባንተ ትዕዛዝ የተፈጠረ አዳም...» ተብሎ ቃሉ ከጥበብ ጋር አንድ ተደርጎ ተወስዷል።

ጥበብንና የኦሪት ሕግን አንድ ዓይነት እና ልዩነት የሌላቸው አድርጎ የሚመለከት አስተሳሰብ ከዚህ ትምህርት ጋር መነፃፀር ይኖርበታል። ይህ አመለካከት በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ በተለይም በመጽሐፈ ሲራክና በአበው ንግግሮች ውስጥ በተደጋጋሚ ይታያል። ለምሳሌ በመጽሐፈ ሲራክ ምዕ.24 ውስጥ ኢያሱ ሲራክ ረዘም ያለ የጥበብ መግለጫ በማቅረብ በቁ.23 ላይ «ይህ ሁሉ ሙሴ ያዘዘን የእግዚአብሔር ሕግ የያዕቆብ ወገኖች ርስት በተጻፈበት...» ይላል። በአበው ንግግሮች 3፡19 ውስጥ «ዓለም የተፈጠረችበት ቃል የተሰጣት እስራኤል የተወደደች ናት» ተብሎ እንደተጠቀሰው

የአሪት ሕግና የእግዚአብሔር ቃል አንድ ናቸው። እነዚህ ዝንባሌዎች ለአንድ የአዲስ ኪዳን ተማሪ የሚሰጡት ጥቅም ግልጽ ነው፤ ይህም ዮሐ 1፡1-18ን አጥንቶ መተርጎም እንዲችል መሠረታዊ መረጃ ያቀርቡለታል። አይሁድ ስለ ጥበብ፥ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ አሪት ሕግ የሚያትቱት ነገር «በሥጋ በተገለጠው ቃል» በኢየሱስ የተፈጸመ መሆኑን ዮሐንስ ይናገራል።

## ኃጢአት

ስለ ኃጢአት ምንጭ በነዚህ ዘመናት ሰፊ ውይይት ተካሂዷል። ለዚህ ጥያቄ የተሰጡት መልሶች የተለያዩ ይሁኑ እንጂ አብዛኛዎቹ ያተኮሩት በአዳም ኃጢአት ላይ ነበር። አንዳንድ ጊዜ ስለዚህ ነገር የምትወቀሰው ሔዋን ስትሆን አልፎ አልፎ አዳምም ተወቅሷል፤ በተቀሩት ወቅቶች ደግሞ ሰይጣን ወይም የወደቁት መላእክትም ጭምር እንኳ ተወቅሰዋል፤ ሲራ.25፡24፤ 1ኛ ዕዝራ 7፡118፤ ጥበ2፡24ና 1ኛ ሄኖክ 10፡7-8። በሌላ በኩል ደግሞ የ2ኛ ባሮክ ጸሐፊ ኃጢአትን የጠነሰሰው አዳም ነው የሚለውን ሐሳብ በመቃወም አዳም በመጀመሪያ ተሳስቶ ከሰው ሁሉ ላይ ድንገተኛ ሞት ቢያስከትልም እንኳ ከእርሱ የተወለዱት እያንዳንዳቸው በራሳቸው ነፍስ ላይ ለሚደርሰው ጭንቀት የተዘጋጁና እንደገናም የወደፊት ክብሮችን ለራሳቸው ለመውሰድ የመረጡ ናቸው፤ ... ስለዚህ የዚህ ነገር መንስኤ አዳም አይደለም፤ እርሱ ማዳን የሚችለው የራሱን ነፍስ ብቻ ነው። እያንዳንዱ ሰው «ለገዛ ራሱ ሕይወት አዳም ነው» በማለት ይናገራል፤ 2ኛ ባሮ.54፡15፥ 19። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደተመለከትነው የኃጢአት ሥርየትን በሚመለከት መሥዋእት ዓበይት መንገዶች ሲሆን፥ መሥዋዕቱም ግቡን እንዲመታ ሥራ በጣም አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ «አባቱን የሚያከብር ልጅ ኃጢአቱ ይሰረይለታል» ና «ምጽዋት ከሞት ታድናለች፤ ከኃጢአት ሁሉ ታነጻለች» የሚሉትን ሁለት ጥቅሶች አወዳድሩ፤ ሲራ.3፡3 ና ጦቢ.ት 12፡9። ጳውሎስ የዚህን ሥርዓት ስሜቶች ክፉኛ ተቃውሟል። በተጨማሪም በነዚህ ጽሑፎች ውስጥ የቅዱሳን ትሩፋት ያስተሰርያል ተብሏል፤ ዕዝ.ሱቱ.8፡28፡29። እንዲሁም ቢያንስ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ የታማኝ አማላጆች ሰማዕትነትም ደግሞ ለኃጢአት ዋጋ በቂ እንደሆነ ተቆጥሯል፤ 4ኛ መቃቢ. 6፡28-29።

## ስነ ምግባር

የሰው ዋና ዓላማ ሕግን መገንዘብና መታዘዝ ነው። አንድ የአሪት ሕግ መምህር፡- «የአሪትን ሕግ ጠንቅቃችሁ ብታከብሩ የተፈጠራችሁት ለዚህ ነውና ይህንን እንደ ትልቅ ነገር አትቁጠሩት» በማለት ተናግሯል፤ የአበ.ንግ.2፡9። የአሪት ሕግ የእግዚአብሔር አጠቃላይ መገለጥ ተደርጎ በተወሰደበት ዘመን ይህ አመለካከት መገኘቱ አስገራሚ አይደለም። ሆኖም አመለካከቱ አንዳንድ ሰዎች ደኅንነት የሚገኘው በተግባር ነው የሚለውን ትምህርት መንፈሳዊ ባልሆነ መንገድ እንዲያስተምሩ ገፋፍቷቸዋል። ለምሳሌ አቂባ የተባለው ሰው እግዚአብሔርን ባለሱቅ አስመስሎ በማቅረብ ሰዎች ሕጉን ቢያከብሩ ሽልማትን ከእርሱ ይቀበላሉ፤ ቢተላለፉ ደግሞ ይቀጣቸዋል ብሎ አስተምሯል፤ የአበ.ንግ. 3፡20።

ሆኖም ከሥነ-ምግባር ይዘት አንጻር ሲታይ ከብሉይ ኪዳን ያነሰ ትምህርት አያቀርብም። በ12ቱ አበው ኪዳኖች ውስጥ «እግዚአብሔርንና ባልንጀራህን ውደድ» የሚለው አስደናቂና የጌታችን ትምህርት ቅድመ መገለጥ የሆነው ምክር በርካታ ጊዜ

ተጽፏል፡ ለምሳሌ የይሳኮር ኪዳን 5፡2። የጋድ ኪዳን የተባለው የዚህ መጽሐፍ አንዱ ክፍል በምዕ.3፡6-7 ውስጥ፡- «እርስ በርሳችሁ ከልብ ተዋደዱ፤ አንድ ሰው ቢበድላችሁ ነገሩን በእርጋታ ከእርሱ ጋር ጨርሱ፤ በነፍሳችሁ ውስጥ ማታለል አይኑር። የበደላችሁ ሰው ንስሐ ቢገባና ቢናዘዝ ይቅር በሉት፤ ጥፋቱን ከካደ ግን የተናገራችሁትን ቃል ይዞ በመማልና በመገዘት የእናንተን ኃጢያት ዕጥፍ ስለሚያደርግባችሁ ከእርሱ ጋር አምባጓሮ አትፍጠሩ፤ ጥፋቱን የካደ ቢሆንም እንኳ ወደ አዕምሮው ሲመለስ ራሱ ስለሚያፍር ወቀሳችሁን ተዉ። ጥፋቱን የካደ ሰው እናንተን ደግሞ ላለመበደል ይጠነቀቃል፤ እንዲያውም ሊያከብራችሁና ከእናንተም ጋር ስምምነት ሊፈጥር ይችል ይሆናል። ሆኖም ይህ ሰው አፍረተቢስ ቢሆንና እናንተንም መበደሉን ባያቋርጥ እንኳ ከልባችሁ ይቅር በሉትና በቀሉን ለእግዚአብሔር ተዉለት» በማለት ከፍተኛ የይቅርታ ትምህርት ያቀርባል።

አንድ ምሁር ይህንን የመሳሰሉት አንዳንድ ምንባቦች ከጌታችን ትምህርቶች ጋር ጎን ለጎን የሚሄዱ በመሆናቸው ጌታችን ኪዳኖች የተሰኙትን ጽሑፎች አጥንቶ ተጠቅሞባቸዋል ወደሚል አስተሳሰብ አምርቷል። አባባሉ ትክክል ሊሆን ይችላል፤ ይሁን እንጂ እርግጠኞች መሆን አንችልም። ስብከት የሕይወት እንጀራ በሆነበት በዚያን ዘመን ይኖሩ በነበሩት አይሁድ ሁኔታ ምሳሌያዊ ንግግሮች የማንም ሰው የግል ንብረት ሊሆኑ አይችሉም። ከዚህም በላይ ኪዳኖችን ለክርስቲያን በሚስማማ አቀራረብ መገኘታቸው በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጨምረዋል አያሰኝም፤ ከዚህ ይልቅ የአዲስ ኪዳን ትምህርት ይገኝባቸዋል ማለቱ ሳይሻል አይቀርም።

## መጨረሻ ስለሚሆኑ ነገሮች የተጻፈ ትምህርት

በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በነበረው ዘመን ከፍተኛ የትምህርት ለውጥ የተደረገበት ርዕስ ይህ ነው። የዚህ ትምህርት ለውጥ ጉልህ ሆኖ የሚታወቀው በተለይ ለሚከተሉት ሦስት ጥያቄዎች ባቀረባቸው መልሶች ነው። እነርሱም፡-

1. ከሞት ባሻገር የሰው ሕልውና ምን ይመስላል?

2. የእግዚአብሔር መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው?

3. የመሢሑ አመጣጥ እንዴት ነው? የሚሉ ናቸው።

ከሞት ባሻገር የሰው ሕልውና ምን ይመስላል? የምንችለውን ያህል ለመናገር የቀድሞ እስራኤላውያንም እንኳ ሰው ከሞት ባሻገር ሕይወት ሊኖረው እንደሚችል ያምናሉ። ይሁን እንጂ ከሞት ባሻገር እናገኘዋለን ብለው የጠበቁት ሕይወት ያልተብራራ ከመሆኑ በላይ ከአምላካቸው ጋር ባለው የቅርብ ግንኙነት ላይ አላተኮረም። ከዚህ አንፃር ሲታይ መዝሙረኛው በመዝ.88 ላይ ከሞት ባሻገር ያለውን ሕይወት ሲገልጽ፡- ሙታን ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር የማይገናኙበት ሥፍራ አስመስሎ ተናግሯል። አንዳንድ ሰዎች፡- «ወደ ማልመለስበት ሳልሄድ «ዐርፍ ዘንድ ተወኝ» የሚለውን አስተሳሰብ የመሳሰሉ አመለካከቶችን በአዕምሮአቸው ውስጥ በማስቀመጥ፥ ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት ጨርሶ ሕልውና የማይኖርበት አድርገው ይቆጥሩታል፤ መዝ.39፡13።

የእግዚአብሔር ቅዱሳን ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ኅብረት በይበልጥ ባንፀባረቁትና ያገኙትንም ልምድ ከእግዚአብሔር መንግሥት መምጣት እውነተኛነት ጋር ባዛመዱት ቁጥር ስለዚህ ሁኔታ ግልጽ የሆነ ዕውቀት ተገኝቷል። ከዚህ የተነሣ ኢዮብ የዋህ በመሆኑ ከሞት በኋላ የእግዚአብሔርን ቅን ፍርድ እንደሚያይ ያምናል፤ ኢዮብ

19፡25-27። እንዲሁም የመዝ.139 ጸሐፊ፡- «ወደ ሲኦልም ብወርድ አንተ በዚያ አለህ» በማለት ሲኦልም እንኳ እግዚአብሔርን ሊያገደው እንደማይችል አምኗል፤ ቁ.8። በተጨማሪም ደግሞ የመዝ.73 ጸሐፊም እግዚአብሔር ከሞት በኋላ ወዳለው ክብር ጋብዞት ኅብረቱን ከእርሱ ጋር እንደሚቀጥል በናፍቆት ይጠባበቃል፤ ቁ.24-25።

ይህ ዓይነቱ ትምህርት በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ሥፍራ ስለማይገኝ ብዙ የአይሁድ መምህራን ሊቀበሉት አልፈቀዱም። ሰዱቃዊው ኢያሱ ሲራክ የሕይወትህ ዘመን አሥር ዓመት፥ መቶ ወይም ሺህ ይሁን፤ በሲኦል አይመረመርም በማለት ጽፏል፤ ሲራ.4፡41። ይህም ከሞት በኋላ እግዚአብሔር የኃጢአት ቅጣት እንደማይሰጥ በግልጽ የሚደግፍ ዐ.ነገር ነው።

የብሉይ ኪዳንን ትክክለኛ ትምህርት ያሰፈሩት የፈሪሳውያን ቅድመ አያቶች ሐሲዶች ነበሩ። ይህንን በሚመለከት ከጌታችን ትምህርት ጋር ጎን ለጎን የሚሄድ ግሩም ትምህርት በመቃብ.7፡18-19 ውስጥ ይገኛል፤ ይኸውም «ሰዎች ከሙሉ ልባቸው ጽድቅን የመጀመሪያ ሐሳባቸው ቢያደርጉ የቀድሞ አባቶቻችን አብርሃም፥ ይስሐቅና ያዕቆብ እንዳልሞቱና ለእግዚአብሔር በሕይወት እንደሚኖሩ ቢያምኑ የሥጋን ድካም ሊገዙ ይችላሉ» የሚል ነው። በአበው ንግግሮች በምዕ.4፡21 ውስጥ «ይህ ዓለም ወደፊት በሚገለጠው ዓለም ፊት የሚገኝ መተላለፊያ በር ነው፤ ወደ ግብዣ አዳራሽ እንድትገቡ በመተላለፊያ በር ላይ ራሳችሁን አዘጋጁ» የሚለውን የአንድ የአሪት ሕግ መምህር አባባል ይዘን የኢያሱ ሲራክን አባባል ከሚቃረን ትምህርት ላይ ደርሰናል። ከሞት ባሻገር ሕይወት የሚገኝ መሆኑ ይህ የባለ ራዕዮች ቋሚ አመለካከት ነው፤ በአይሁድ እምነትም ውስጥ ይህንን አመለካከት ያስፋፉት እነርሱው ናቸው።

የእግዚአብሔር መንግሥት፡- በዚህ ትምህርት ላይ ሦስት የአስተሳሰብ ክፍሎችን ልናቀርብ እንችላለን። የእግዚአብሔር መንግሥት ምድራዊ መሆኑን የሚገልጡ ምንባቦች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ፤ ለዚህ ነገር ዋናው ማስረጃ ተወዳጅ የሆነው በኢሳ.11፡1-9 ውስጥ የሚገኘው ትንቢት ነው። ቀደም ብሎ የተለያዩ የራዕይ መጻሕፍትን የደረሱት ሰዎች እነዚህን በመሳሰሉ ምንባቦች ላይ ያተኮረ ነበር፤ መንግሥቱን በሚመለከት እነዚህን ትንቢቶች የሥጋን ምኞት በሚቀሰቅሱ መንገድ ተርጉመዋቸዋል። 1ኛ ሄኖክ 10፡17- ጻድቅ እስከ እርጅና ዘመኑ በመልካም ይኖራል፤ አእላፍ ልጆች ይወልዳል፤ የልጆቹም ዘር ሺህ ዕጥፍ ይሆናል፤ እያንዳንዱ መስፈሪያ የወይራ ፍሬ አስር መለኪያ ዘይት ያፈራል፤ ወዘተ ይላል። ፓፒያስ የተባለው ሰው ስለ አንድ ሺው ዘመን የሰጠው መግለጫ ምንጭ ከዚህ ነው።

ኢሳ. 65፡17-22 ስለ ታደሰ ሰማይና ምድር ይናገራል፤ ይሁን እንጂ በሥነ-ምግባራዊና በሥጋዊ መንግሥታት ውስጥ ቃል በቃል የሚተረጎመው የቱን ያህል እንደሆነ አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። ሆኖም አንዳንድ የመጀመሪያዎቹን መቶ ዓክልበና ዓ.ም. የራዕይ መጻሕፍት የደረሱ ሰዎች የመሢሑ መንግሥት በምድር ላይ ቢመሠረትም እንኳ ለአጭር ወቅት እንደሆነና ለሰማያት ዘላለማዊ መንግሥት ሥፍራውን እንደሚለቅ ይገልጻሉ። ይህ አስተሳሰብ በ2ኛ ሄኖክ ውስጥ የዓለም ታሪክ 7000 ዓመታት እንደሚፈጅ የመጨረሻዎቹ 1000 ዓመታት የአንድ ሺው ዘመን መንግሥት እንደሚሆኑና ከዚህ በኋላ ዘላለማዊው መንግሥት አዲስ ፍጥረት እንደሚጀምር ከሚናገረው ሐሳብ ጋር ተያይዟል፤ 2ኛ ሄኖክ 32፡2-33፡2። ለዚህ ጸሐፊ የመሢሁ ጊዜያዊ መንግሥት ትልቅ ዋጋ እንዳለው ግልጽ ነው። ይሁንና በዕዝራ ሱቱኤል ውስጥ ጸሐፊው ለዚህ ዓለም ያለውን ክፉ አስተሳሰብ በመመልከት ዋጋ ዝቅ ያለ ተደርጎ

ተወስዷል። የመሢሁ ጊዜያዊ መንግሥት ወደ 400 ዓመታት ዝቅ ያለ ሲሆን በዚህ ዘመንም መጨረሻ ላይ መሢሁና ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ ይሞታል፤ ዕዝ.ሱቱ.7፡29።

ከዕዝራ ሱቱኤል አመለካከት እንጻር ሲታይ አንዳንድ የራዕይ መጻሕፍት የደረሱ ሰዎች የመሢሁን ጊዜያዊ መንግሥት ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ጨርሰው ማስቀረታቸውና በአዲሱ ሰማይ ላይ የሚሆነውን ዘላለማዊ መንግሥት ብቻ መጠባበቃቸው አያስደንቅም። የ2ኛ ባርክ ጸሐፊ ያቀረበው ይህንን አንድ ወጥ የሆነ ትውፊትን መጠበቅ ነው። ይህቺ ምድር ለእግዚአብሔር እንደማትገባ ስለተሰማው:- «አሁን ያለው ሁሉ ምናምንቴ ነው፤ ወደፊት የሚሆነው ግን በጣም ታላቅ ነው። በሰባሽ የሆነ ነገር ሁሉ ያልፋል፤ የሚሞት ሁሉ ተለይቶት ይሄዳል፤ በክፋት የተበከለው የአሁኑ ዘመን ሁሉ ይረሳል፤ ጨርሶም አይታወስም» በማለት ይገልጸዋል፤ 2ኛ ባሮ.44፡8።

የመንግሥቱ ባሕሪይ ይህንን ይመስላል ተብሎ የተወሰደው አመለካከት የትኛውም ቢሆን አብዛኛው ጊዜ አመጣጡ ልክ በዳን.2 ውስጥ እንደተጠቀሰው የናቡከደነፆር ሕልም ዓይነት እንደሆነ ታስቧል። ሆኖም ኩፋሌ 33ንና 2ኛ ባሮ. 73-74ን በመሳሰሉ አንዳንድ መጻሕፍት ውስጥ የመንግሥቱ በሙላት መገለጥ የሚሆነው ቀስ በቀስ ብቻ እንደሆነ እንመለከታለን። በመጽሐፈ ኩፋሌ ውስጥ የአሪት ሕግ በይበልጥ በተጠናና ሰዎች በታዘዙት ቁጥር መንግሥቱ የማያቋርጥ ሙላት ላይ እንደሚደርስ ተጽፏል።

እንዲሁም የራዕይ መጻሕፍትን የደረሱ ሰዎች ሁሉ ራሳቸውን በመጨረሻው ዘመን እንዳሉ በመቁጠር መንግሥቱ በቶሎ እንደሚገለጥ ተጠባብቀዋል። ይሁን እንጂ በበርካታ ጽሑፎች ውስጥ ታላቁ ቀን በንስሐ እየተፋጠነ እንደሚቀርብ ተገልጿል። «እስራኤል ንስሐ በምትገባበት ቀን የጠላት መንግሥት ያከትማል» የዳን. ኪዳን 6፡4። በሙሴ ንጥቀት ምዕ.1፡18 ውስጥ የመጨረሻው ቀን «እግዚአብሔር የዘመናትን ፍጻሜ በሙላት የሚገልጥበት የንስሐ ቀን» ተብሎ ተጠርቷል።

እነዚህ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የቀረቡ ልዩ ልዩ ትርጉሞች የሃይማኖት ተከታዮች ከሞት ባሻገር ስላላቸው ሕይወት የሚያቀርቧቸውን አሳቦች የግድ ይለውጧቸዋል። የእግዚአብሔር መንግሥት ዓላማ ያለው መንግሥቱን በማቋቋም ላይ ስለሆነ ይህ ዓላማ ያቀፈው የመጨረሻውን ዘመን ትውልድ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ሁሉ መሆኑ ከጥንት ጀምሮ የታወቀ ነበር። ስለዚህ የትንሣኤ ትምህርት ግልጽ የሆነ ነጥብ ላይ ደርሷል። ይህ ትምህርት በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኘው በኢሳ.26፡19ና በዳን.12፡3 ውስጥ ሲሆን ለውጦች አሁንም ተደርገዋል። ሆኖም ይሆናል ተብሎ የተጠበቀው ትንሣኤ የምድራዊ መንግሥት ሐሴት ከሆነ የትንሣኤ አካል ከአሁኑ አካል ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ እንደሚኖረው አያጠራጥርም፤ ስለዚህ በሲቢሊን ራዕዮች 3፡179-192 ውስጥ «እግዚአብሔር የሰዎችን አጥንትና አመድ መልሶ ያበጀውና ሙታን ቀድሞ እንደነበሩ ሆነው ይነሣሉ» የሚል ሐሳብ ይገኛል። በእርግጥ ይህንን የመሰለ ትንሣኤ በመንግሥቱ መጀመሪያ ላይ ይሆናል። ይሁን እንጂ የመሢሑ መንግሥት ጊዜያዊ ይሆናል ተብሎ ከተጠበቀ ትንሳኤው ይህ ዘመን እስኪፈፀም ድረስ ይቆያል። እግዚአብሔር ለአዳም «በዳግም መምጫዬ ወቅት» በማለት በ7000ዎቹ ዓመታት የምድር ታሪክ መጨረሻ ላይ «ከምድር እወስድሃለሁ» ብሎ በነገረው ሥፍራ በሄኖክ ምስጢራት 32፡1 ውስጥም የምናገኘው ሁኔታ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ይህ ጸሐፊ ትንሣኤ ቁሳዊ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊም እንደሆነ የሚያስብ ይመስላል፤

ስለዚህ በሄኖክ ምዕ.22፡8 ላይ እግዚአብሔር ሚካኤልን «ሂድና የሄኖክን ምድራዊ ልብሶች አውልቅለት፤ በጣፋጭ ዘይቱም ቀባውና የክብር ልብሶቼን አልብሰው» ብሎታል። የመጽሐፈ ጥበብን ጸሐፊ የመሳሰሉ ሌሎች ጸሐፊዎች እንዲሁም የመንግሥቱን በምድር ላይ መገለጥ ያልጠበቁ ሰዎች ትንሣኤ የሚሆነው ወዲያው ሰው ከሞተ በኋላ በሞት ላይ እንደሆነ አልፎ አልፎ ገምተዋል። በእርግጥም የመጽሐፈ ጥበብ ጸሐፊ ቢያንስ በጻድቃን ላይ የግሪክ አስተሳሰብ ፅንሰ ሐሳቦች ይታይበታል። ሆኖም ይህ አስተሳሰብ ከአይሁድ እምነት ጋር ተዛማጅ መስሎ ስለማይታይ በአጠቃላይ ተቀባይነት አላገኘም።

## መሢሑ

መሢሁ በብዙ የብሉይ ኪዳን ነቢያት መጻሕፍት ለምሳሌ በአሞጽ፥ በሶፎንያስ፥ በናሆም፥ በዕንባቆም፥ በኢዩኤልና ምናልባትም ደግሞ በዳንኤል ውስጥ አልተጠቀሰም። እንዲሁም በበርካታ የአዋልድ መጻሕፍትም ውስጥ ማለት በአራቱ መቃብያን፥ በዮዲት፥ በጦቢት፥ በ1ኛ ባሮክ፥ በጥበብ፥ በሙሴ ንጥቀትና በ2ኛ ባሮክ ውስጥ ስሙ አይገኝም። በዚህ መሠረት አንድ ምሁር፡- «በአይሁድ ትንቢትና ራዕይ ነክ ጽሑፎች ውስጥ መሢሁ ከመንግሥቱ ጋር የተጣበቀ ግንኙነት የለውም የሚለው ሐሳብ ይቀጥላል» በማለት አስተያየቱን ይሰነዝራል። ይህ ግምት አጠራጣሪ ቢሆንም እንኳ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ውስጥ ሁሉ እነዚህ ጸሐፊዎች የመሢሁን መምጣት አለመጥቀሳቸው አይሁድ ስለመሢሁ መምጣት የነበራቸውን እምነት ተቃውመዋል ለማለት አጥጋቢ ማስረጃ ባይሆንም የዚህ ምሁር ሐሳብ በአጠቃላይ ተቀባይነት አለው። በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የመጨረሻ ስለሚሆኑ ነገሮች የተጻፈው ትምህርት መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት ለመሢሁ የተሰጠው ትኩረት ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የመጨረሻ ነገሮች ትምህርት ሙሉ በሙሉ ከክርስቶስ ማንነትና ከሥራው ጋር የተጣመረ ነው።

መሢሁ በመንግሥቱ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ በሚይዝባቸው የብሉይ ኪዳን ምንባቦች ውስጥ የራሱን ድርሻ በቅጡ ማበርከት የሚጀምረው መንግሥቱ ከተቋቋመ በኋላ እንደሆነ ነው፤ መንግሥቱንም የሚያቋቁመው እርሱ ራሱ አይደለም። መዝ.110፡1- «እግዚአብሔር ጌታዬን፡- ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» በማለት መሢሁ በመንግሥቱ ውስጥ ያለውን ሥፍራ ግልጽ ያደርገዋል። እንዲሁም በአብዛኞዎቹ ራዕይ-ነክ ጽሑፎች ውስጥ መሢሁ መንግሥቱ እስከሚመሠረትበት ወቅት ድረስ እንቅስቃሴውን አይጀምርም። «የሄኖክ አምሳያዎች» የተባለው ጽሑፍ ደግሞ ከፍ ብሎ ከቀረበው ጋር የማይስማማ ስለሆነ ወደፊት እንመለከተዋለን።

በራዕይ-ነክ ጽሑፎች ውስጥ ልክ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንደተጠቀሰው በአብዛኛው መሢሑ ይመጣል የተባለው ከዳዊት ዘር ነው። ይሁን እንጂ በአሥራ ሁለቱ አበው ኪዳኖች ውስጥ ደኅንነት ይነሣል የተባለው ከሌዊና ከይሁዳ ወገኖች እንጂ ከይሁዳ ብቻ ስላይደለ ግራ የሚያጋባ ፅንሰ-ሐሳብ ያጋጥመናል። አብዛኞቹ የጽሑፉ አብራሪዎች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሢሁ እንደሚወጣ የተነገረው ከሌዊ ዘር ነው በማለት አጥብቀው ይናገራሉ፤ በሮቤል ኪዳን 6፡7-12 ውስጥም የምንመለከተው ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ሁኔታ ነው። በይሁዳ ኪዳን 22ና 24 ውስጥ መሲሁ ከይሁዳ ነገድ እንደሚነሣ መነገሩ የዚያኑ ያህል ግልጽ ነው። ከዚህም በላይ የኪዳኖቹን ቅንብር ትርጉም

ከተቀበልን ደኅንነት የሚነሣው ከሌዊና ከይሁዳ ወገኖች እንጂ ከአንድ ነገድ ብቻ አይደለም።

ተስማሚ የሆነው አንድ አተጋቢ ትርጉም ይህ ጸሐፊ ይነሣሉ ብሎ የጠበቃቸው ሁለት መሢሖችን እንጂ አንድ መሢህ ብቻ አይደለም የሚለው ይመስላል። የዚህ አስደናቂ አመለካከት መንስኤ የሌዊ ነገድ አካል የነበሩት የመቃባውያን መሪዎች የጀግንነት ውጤት ብቻ ሳይሆን ጸሐፊው ከክህነት ጋር ካያያዘው ጥቅም የተነሣ ነው። ይሁዳ «እግዚአብሔር ለኔ መንግሥትን፣ ለሌዊ ክህነትን ሰጥቷል፤ እንዲሁም መንግሥቱን ከክህነቱ በታች አቁሞታል... ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ የእግዚአብሔርም ክህነት ከምድራዊ አገዛዝ የላቀ ነው» ብሏል፤ የይሁዳ ኪዳን 21፡1። ይህ ለየት ያለ ትርጉም በጌታችን መወለጃ ዘመን አካባቢ መመንጨቱ ዋናው ሥራው ሥርየትን ለማስገኘት ለሆነው ለመሢሑ በአይሁዶች መካከል እንዲሰብክ መድረክ አዘጋጅቶለት ነበር ለማለት እንችላለን።

በኩምራን ጽሑፎች ውስጥ መሢሕ የሚል ቃል በነጠላ ተጠቅሶ ሲታይ የሚያመለክተው ከዳዊት ዘር የሚነሣውን መሢህ ነው፤ ይሁንና አልፎ አልፎ «አሮናዊና እስራኤላዊ መሢሖች» የሚል ሐረግ ስለሚገኝ አንድ ካህናዊና ሌላ ክህነት ያልተቀበለ ሁለት መሢሖች ይመጣሉ ብለው የተጠባበቁ ይመስላል። በአዲሱ መንግሥት ውስጥ መሪ የሚሆነው ካህናዊው መሢሕ ነው። በአዲሱ የሕዝቅኤል መንግሥት ውስጥ የዳዊት ዘር የሆነው «አለቃ» የካህናዊው አለቃ የበታች እንደሚሆን ሁሉ ክህነት ያልተቀበለው መሢሕም የካህናዊው መሢሕ ረዳት ይሆናል። ከነዚህ ሁለት የተቀቡ መሢሖች ጋር በመጨረሻው ዘመን እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ እንደሚነሣ የኩምራን ሕብረተሰብ ይጠባበቅ ነበር፤ ዘዳ.18፡15።

የሄኖክ አምሳያዎች በተባለው ጽሑፍ ውስጥ ከትውፊታዊው የመሢሑ ምሳሌ በጣም የራቀ አመለካከት ቀርቧል፤ 1ኛ ሄኖክ 37-71። መሢሑ ሰብዓዊ ፍጡር ብቻ አይደለም፤ ከሰው ርቆ የሚኖር፤ አስቀድሞ የነበረ፤ ከፍጥረታት ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ ያለና በእግዚአብሔር ፊንታ ለመምራት ብቻ ሳይሆን መንግሥቱም ለማቋቋም በመጨረሻው ዘመን የሚገለጥ ነው። ማንነቱ በውል ባይጠቀስም ከጻድቃን ሕብረተሰብና ከእግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ ጋር በጣም የተዛመደ ነው። እንዲሁም በአንዳንድ ዕጹብ ድንቅ በሆኑ ጻድቃን ሊመሰል የሚችል ሲሆን በ1ኛ ሄኖ.71፡14 ውስጥ በመጨረሻው የፍርድ ወቅት በክፉዎች ላይ እንዲፈርድ መለኮታዊ ሹመት በተሰጠው በሄኖክ ተመስሏል።

አንድ ምሁር ባቀረበው መሠረት ጻድቁ፥ የተመረጠውና የሰው ልጅ የተሰኙት የኢየሱስ ማዕረጎች ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚመጣው አዳኝ የተሰጡት በሄኖክ ጽሑፍ ውስጥ ነው፤ 1ኛ ሄኖ.52፡4፤ 38፡2፤ 45፡3-4፤ 46፡1-6። እነዚህ ማመሳከሪያዎ ሁሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥም ይገኛሉ። እነዚህ ጥቅሶች (ጽሑፎች) ወደፊት ስለሚመጣው አዳኝ የሰጡዋቸው ማመሳከሪያዎች እግዚአብሔር ለማዳን ዓላማው ሲል ያካሄደው ከነበረው ሂደት ጋር የሚስማሙ ማረጋገጫ ሐሳብን ይዘው ስለሚገኙ የደኅንነቱ ታሪካዊ ሂደት አካልና ክፍል በመሆናቸው ጠቃሚ ጽሑፎች ናቸው። እነዚህ ጽሑፎች ወደፊት ለሚመጣው አዳኝ ከሰጧቸው ማመሳከሪያዎች ጋር እግዚአብሔር ለማዳን ዓላማው ሊጠቀምበት ያካሄደው የነበረው የአጠቃላዩ ታሪካዊ ሁኔታ አካልና የማይለያዩ ክፍሎች በመሆናቸው ጠቃሚ ነበሩ።

## ማሳሰቢያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ መለመድ አለባቸው ብለን የገመትናቸውን አዳዲስ ቃላት ተጠቅመናል፤ ነገር ግን ከነዚህ መካከል ለአንባቢ ግልጽ ላይሆኑ ይችላሉ ያልናቸውን የሁለት ቃላት ትርጉም አቅርበናል።

1. አራሚ - ጣኦት አምላኪ

2. ትውፊት - ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ አፈ ታሪክ

# በሁለቱ ኪዳኖች መካከል የነበረው ዘመን

የብሉይ ኪዳን ታሪክ የሚያከትመው የፋርስ መንግሥት ጥብቅ አገዛዝ በምዕራብ እስያ ማለት በግሪክ፥ ሶርያና እስራኤል በሰፈነበት ወቅት ነው። ብሉይ ኪዳን በስም የሚጠቅሰው የመጨረሻ ንጉሥ የፋርሱን ዳርዮስን ነው። ይህ ንጉሥ ከ423 - 404 ዓክልበ የነገሠው ዳግማዊ ዳርዮስ ወይም ከ336 -331 የነገሠው ሣልሳዊ ዳርዮስ ሊሆን ይችላል፤ ነሀ.12፡22። አዲስ ኪዳንን ደግሞ ስንከፍት የሜዲትራኒያን ባሕር አካባቢ በሙሉ አንድ ሌላ ኃያል መንግሥት ሲገዛ እንመለከታለን። ሉቃስ የኢየሱስን ልደት ከ27 ዓክልበ -14 ዓ.ም. ከገዛው ከሮም የመጀመሪያ ገዢ ከአውጉስጦስ ቄሣር «በዚያ ዘመን ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ትእዛዝ ወጣች» ከሚለው ትእዛዝ ጋር ያያይዘዋል፤ ሉቃስ 2፡1። እንዲሁም የአጥማቂው ዮሐንስ አገልግሎት ከ14-37 ዓ.ም. ከአውጉስጦስ ቄሣር በኋላ «ጢባርዮስ ቄሣር በነገሠ በ15ኛው ዓመት» እንደሆነ ተጠቅሷል፤ ሉቃስ 3፡1። ኢየሱስ የሞት ቅጣት የተፈረደበት በሮማዊ ዳኛ ሲሆን የሞት ፍርዱም የተፈጸመበት በሮማውያን የአገዳደል ደንብ ነበር። የክርስትና መልእክት በሜዲትራኒያን አካባቢ እጅግ በተፋጠነ አኳኋን የተስፋፋው ዜግነቱ ሮማዊ በሆነ ሰው ነበር። አዲስ ኪዳንም የሚደመድመው የኋላ ኋላ የሮምን አገዛዝ የምታሸንፈውን ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት በዛቻ ላይ እንዳለ ነው።

በፋርስ፥ የመጨረሻ ንጉሥና የሮማውያን ግዛት በቅርብ ምሥራቅ አገሮች ውስጥ መንሰራፋት ጅማሬ መካከል፥ ይህ አካባቢ በታላቁ እስክንድርና በተከታዮቹ ጨቋኝ የግሪክና የመቄዶናያን አገዛዝ ቁጥጥር ሥር ነበር። ይህንን ጨቋኝ መንግሥት የሚጠቅሱ አንዳንድ ራዕይ-ነክ ግንዛቤዎች በዳንኤልና በአንድ ወይም በሁለት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ፤ ይሁንና የአዋልድ መጻሕፍት ራሳቸው እንኳ በመቃብያን መጻሕፍት ከተዳሰሰው ከ2ኛ መቶ ዓክልበ አጭር ዘመን ሌላ ስለ ግሪክና መቄዶንያውያን መሪዎች የሚነግሩን ነገር በጣም ትንሽ ነው። ቢሆንም በሁለቱ ኪዳኖች መካከል ከነበረው ዘመን አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦች ጋር ካልተዋወቅን አዲስ ኪዳንን ራሱን በቅጡ ልንረዳው ያዳግተናል።

በ331 ዓክልበ ታላቁ እስክንድር የፋርስ መንግሥትን ድል መምታት ለሰማሪያ ወይም ለይሁዳ ምንም ሕገ-መንግሥታዊ ለውጥ አላስገኘላቸውም። ቀድሞ ይመሩ የነበረው በፋርስ ገዢዎች ሲሆን አሁን ግን በእነርሱ ፈንታ የግሪክና መቄዶንያውያን ገዢዎች በመምራት ላይ ነበሩ፤ ግብር የሚከፈለውም በቀድሞው ፈንታ ለአዲሱ ገዢ ነበር። በፋርስ ግዛት ውስጥ በሰፊው ተሰራጭተው የነበሩት የተበተኑት አይሁድ አዳዲስ ማዕከሎችን በተለይም እስክንድርያንና ሰሜን አፍሪካን አግኝተዋል። ብዙም ሳይቆይ በነዚህ አይሁዶች መካከል የግሪክ ባሕል ነፀብራቆች ተገልጠዋል። እነዚህ የግሪክ ስልጣኔ ነፀብራቆች ከአንዳንድ አቅጣጫዎች ሲታዩ መልካም ነበሩ። በተለይ የእስራኤል አምላክ

ዕውቀት በአሕዛብ ዓለም በቀላሉ ሊደረስበት እንዲችል በእስክንድርያ በ3ኛውና በ2ኛ ዓክልበ በግሪክ ተናጋሪ አይሁዶች መካከል ፔንታቱክ እንዲሁም ሌሎቹ የብሉይ ኪዳን ጽሑፎች ወደ ግሪክ መተርጎማቸውን ልንገነዘብ እንችላለን። በሌላ በኩል ደግሞ ከአራሚ እምነት ጋር ጨርሶ ሊለያዩ በማይቻል አኳኋን የተቀላለፈውንና ከሌላም አቅጣጫዎች ሲታይ በእግዚአብሔር ልዩ ሕዝብና በጎረቤቶቻቸው መካከል ያለውን ልዩነት የሚያደበዝዘውን የግሪክ ሥልጣኔ ዘመን ባህልን የመቅዳት ዝንባሌ ይታይ ነበር። የተከበረ የአይሁድ ቤተሰብ በግሪክ ሥልጣኔ ዘመን እንዴት በግሪክ መጥፎ ኑሮ ውስጥ ሊዘፈቅ እንደቻለ ጆሲፈስ ገልጿል። አንድ በጣም የተከበረና የታወቀ ቶቢያዳ የተባለው ቤተሰብ አባላት በመጀመሪያ በፕቶሌማውያን ከዚያም ቀጥለው በሴሌውሲዳውያን አገዛዝ ዘመን ውስጥ ከግሪኮች ጋር በመመሳጠር በግብር ሰብሳቢነት ሰበብ ከገዛ ወገናቸው ገንዘብ በመንጠቅ በልጽገዋል።

የታላቁ እስክንድርን ግዛት ከወረሱት ንጉሣዊ ዘሮች መካከል በእስራኤል ታሪክ ላይ ሀቢይ ለውጥ ያስከተሉት ሁለት ናቸው። እነርሱም፡- በግብፅ የነበሩት ፕቶሌማውያንና ሦሪያውያን፡ እንዲሁም ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ የነበረውን ምድር ይገዙ የነበሩት ሴሌውሲዳውያን ናቸው። ከ323 - 198 ዓክልበ የፕቶሌማውያን አገዛዝ ከግብፅ ጀምሮ እስያን በመጠቅለል የሊባኖስን ተራራና የፊንቄን ድንበር ይዞ ይሁዳንና ሰማሪያን ጨምሮ ተስፋፍቶ ነበር። በ198 ዓክልበ ሴሌውሲዳውያን በዮርዳኖስ ወንዝ ምንጮች አጠገብ ቢፓኒዮን ላይ የተጎናጸፉት ድል ይሁዳንና ሰማሪያን በእስክድሪያ ፈንታ ለአንጾኪያ ገባር አድርጓቸዋል ማለት ነው። ከ8 ዓመት በኋላ የሴሌውሲዳውያን ንጉሥ ሳልሳዊ አንቲዮክስ በ190 ዓክልበ በማግኔሺያ፥ በሮማውያን እጅ የተሸነፈ ሲሆን የተጫነበት የማካካሻ ቅጣት አይሁድን ጨምሮ በሥሩ በነበሩት ተገዢዎች ላይ ከፍተኛ ግብር ጨምሮባቸዋል። የአንቲዮክስ ልጅ አንቲዮክስ 4ኛ በ169 እና 168 ዓክልበ ዘመቻዎች አማካኝነት የመንግሥቱን የበላይነት ሥልጣን በግብፅ ላይ በመጫን ሁኔታውን ለማስተካከል ሲሞክር ሮማውያን እነዚህን እንቅስቃሴዎች እንዲተው አስገድደውታል። ስለዚህ በመንግሥቱ በስተሰሜን ምዕራብ የምትገኘው ይሁዳ አሁን ጥቅም የምታስገኝ የጦርነት ቁልፍ ሥፍራ ሆነች። እንዲሁም በይሁዳ የሚገኙትን ተገዢዎቹን እንዲጠራጠራቸው የሚያደርግ ከፍተኛ ምክንያትም ነበረው። ጥበብ በሌላቸው አማካሪዎች ምክር ተነሣሥቶ የአይሁድን ብሔርነትና የሐይማኖት መለያቸውን ለማጥፋት ቆርጦ ተነሥቶ ነበር። የዚህ መመሪያ የመጨረሻ ግብ የአራሚ አትል እምነት ማለት የዚዮስ ኦሎምፒዮስ አምልኮ በ167 ዓክልበ በታኅሣሥ ወር በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ መግባቱ ነበር፤ አይሁዶች ጥቂት የፊደል ለውጥ በማድረግ የግሪክ አምላክ የጥፋት ርኩሰት ብለው ጠርተውታል። እንዲሁም በገሪዛን የሚገኘው የሰማሪያውያን ቤተ መቅደስም በተመሳሳይ ሁኔታ ወደ ዜዩስ ዜኒዮስ የአምልኮ ሥፍራነት ተለውጧል።

በዚህም ምክንያት ሃይማኖታቸው ሲሻር ብዙ ለሃይማኖታቸው የሚቀኑ አይሁዶች ወዲያውኑ በሰማዕትነት አልፈዋል። ሌሎቹ ደግሞ በሴሌውሲዳውያን መሪዎቻቸው ላይ የተቃውሞ ክንዳቸውን አስተባብረው አንሥተዋል። ከነዚህም ሰዎች መካከል ካህን በሆነው በማታትያስና በአምስት ልጆቹ የሚመሩት የሐስሞናውያን ቤተሰብ አባላት ይገኙባቸዋል። ከአምስቱ ልጆች መካከል ይሁዳ መቄባስ የተባለው ተወዳዳሪ ያልነበረው፥ በተፈጥሮው ሰዎችን የመምራት ተሰጥኦ ያለውና በደፈጣ ውጊያ የላቀ ችሎታ የነበረው ሰው ነበር። ጠንካራ ተዋጊ በመሆኑ መቄባስ ማለት መዶሻ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶታል። በአንቲኦክስ 4ኛ ኃይሎች ላይ የተጎናጸፈው የመጀመሪያው

ድል በእስራኤል ውስጥ የሚገኘውን በዕብራይስጥ ሐሲዲም የተባለውን የሃይማኖት ክፍል ጨምሮ ለሕዝባዊና ለሃይማኖታዊ ሕልውናቸው አስጊ የሆነውን የወቅቱን ዛቻ በላላ አኳኋን ብቻ መቋቋም በቂ አይደለም ብለው የገመቱትን ብዙዎች ወገኖቹን በእርሱ መሪነት ሥር እንዲሆኑ አድርጎለታል። አንቲአከስ ሰፌ ሠራዊት ልኮባቸው ነበር፤ ሆኖም በይሁዳና በወታደሮቹ ያለተጠበቁ የጦር ስልቶች አማካኝነት ድባቅ መትተዋቸዋል። አንቲአከስ የአሠራር ስልቱ እንደከሸፈ በግልጽ ስለተረዳ ይሁዳ ሰላም ለመፍጠር ተወካዮቹን ወደ አንጾኪያ እንዲልክ ተጋብዞ ነበር። አንቲዮከስ በስተምሥራቅ በኩል የተገነጠሉትን ወረዳዎች እንደገና ለመውጋት ወታደራዊ ዕቅዶችን አውጥቶ ስለነበር በግብፃውያን ድንበር በኩል አንድ ስምምነት ላይ መድረስ ይጠቅመው ነበር። የአይሁድ መሠረታዊ መነሻ ነጥቦች በኃይማኖት አኗኗራቸው ላይ የተደረገባቸውን እገዳ ጨርሶ እንዲነሣ ለማድረግ ነበር። ይህም ሁኔታ ተሽሮ አይሁድ እንደገና የአባቶቻቸውን ሃይማኖት እንዲያመልኩ ነፃነት አግኝተዋል። የዚህ እገዳ መሻር ወዲያው ወደ ቤተ መቅደሱ ገብቶ የነበረውን የጣኦት አምልኮ አስወጥቶ ቤተ መቅደሱን ማንጻትና ለዘላቂው የእስራኤል አምላክ አምልኮ እድሳት እንዲቀጥል አድርጓል። በዮሐ፡ 10፡22 ውስጥ እንደተጠቀሰው በ164 ዓክልበ መጨረሻ ላይ የተደረገው እና ከዚያም ወቅት በኋላ በየዓመቱ ለመታሰቢያ ይከበር የነበረው የመቅደስ መታደስ በዓል እንዲቀጥል የተደረገ ቢሆን ለዚህም ግሪኮች ዝም ያሉት ይሁዳ መቄባስና እንዲአከስ በተፈራረሙት ውስጥ ሰፍሮ ባይገኝም ነገሩ መቼም የማይቀር መሆኑን ስለተረዱት ነበር።

ይህም ሆኖ ይሁዳና ተከታዮቹ እንደገና የተገኘው የሃይማኖት ነፃነት አላረካቸውም። ይህንን ድል በመሣሪያዎች ኃይል ከተጎናፀፉ በኋላ አስተዳደራዊ ነፃነታቸውን ለማግኘት ትግላቸውን ቀጥለዋል። ከቤተ መቅደሱ መታደስ በኋላ የቤተ መንግሥቱ ዘበኞች ይሰማሩበት ከነበረው ምሽግ ፊት ለፊት ያለው የቤተ መቅደሱ ጋራ የተመሸገ ሲሆን ይሁዳ መቄባስ ወደ ገሊላ፥ ዮርዳኖስ አካባቢና በብቸኝነት ያሉ አይሁድ ወደሚገኙባቸው ሌሎች ሥፍራዎች ሁሉ የታጠቁ ጓዶችን በመላክ በእርሱ ኃይላት ቁጥጥር ሥር ወደ ነበሩት ሥጋት የሌለባቸው አካባቢዎች ሊያስመጣቸው ችሏል።

የሴሌውሲዳውያን መንግሥት ማለት እነአንቲአከስ ይህን የመሳሰሉትን ተከታታይ የሆኑ የጠላትነት ድርጊቶች ቸል ብለው ሊያልፉ ስላልቻሉ በይሁዳ መቄባስ ላይ ተጨማሪ ሠራዊቶች አዝምተውበታል። ይሁዳ መቄባስም በ160 ዓክልበ በመጋቢት ገደማ በተደረገው ጦርነት ሳቢያ የሞተ ሲሆን፥ እርሱ ያካሄደው የነበረውም ዓላማ ለጊዜው ያከተመለት መስሎ ታይቶ ነበር። ይሁን እንጂ አንዳንድ የዘመኑ አጋጣሚዎች ተከታዮቹን ሊያበረታታው ችሏል። በተለይም በ163 ዓክልበ አንቲዩከስ 4ኛ ስለሞተ በሴሌውሲዳውያን ግዛት ውስጥ ዙፋኑን መውረስ ይገባናል በሚሉት ሰዎችና በተቀናቃኞቻቸው መካከል አልፎ አልፎ ለረጅም ዘመን የእርስ በርስ ጦርነት አስከትሏል። ይህም በመሆኑ በይሁዳ መቄባስ ምትክ የቡድን መሪነትን የተረከበው ወንድሙ ዮናታን የተመቻቹ ጊዜያት እስኪያገኝ ድረስ በማድፈጥ ቆይቶ ስለነበረ ወቅቱ ሲደርስ ዘዴ በተሞላው አቀራረብ ውጊያውን ድል አድርጎ አስደናቂ ዕድገት ለማሳየት ቻለ። ከ11 ዓመት በኋላ በ152 ዓክልበ የሴሊውሲዳውያን ዙፋን ይገባኛል፥ የአንቲዮከስ 4ኛ ልጅ ነኝ፥ የሚለው ልጅነቱ አጠራጣሪ የሆነው እስክንድር በላስ ዮናታን የእርሱን ሐሳብ ለመደገፍ ቃል ከገባለት በኋላ በይሁዳ ያለውን ወታደራዊ ኃይል እንዲያጠናክርና ዮናታን የአይሁድ ሊቀ ካህናት እንዲሆን ተስማሙ።

የእስክንድር በላስ «አባት» አንቲዮክስ 4ኛ በመጨረሻ ላይ ሐስሞናውያን እንዲያምጹ ያደረጋቸውን የአይሁድን የጥንት ልማድ ማውገዝ በመጀመሩ የሳዶቅ ቤተሰብ የሆኑትን ሊቃነ ካህናት ሽሮ በገዛ ፈቃዱ ሌሎች ሊቃነ ካህናት በመሾሙ ነበር። አሁን ግን ጉድ ፈልቷል! ይኸውም ለሃይማኖታቸው ጥራት እስከ ሞት የተጋደሉትን የሐስሞናውያንን ቤተሰብ የሥልጣኑ መሠረት ለማድረግ ሲል የአንቲዮክስ 4ኛ ልጅና ወራሽ ነኝ ካለው ሰው እጅ የሊቀ ክህንነቱን ማዕረግ በመቀበላቸው ነበር፤ ይህንንም በመፈጸማቸው የትግላቸውን ክቡር ዓላማዎች አንቋሸሸዋል።

በሐስሞናውያን ብርታት ብቻ ሃይማኖታዊ ነፃነት እንደገና የሚገኝ መስሎ በታየበት ወቅት ለሐስሞናውያን ዕርዳታቸውን ለግሠው የነበሩት ሃይማኖተኛ ቡድኖች የተፈለገው ግብ ላይ ሲደርሱ መደሰታቸውን አቁመው በሐስሞናውያን ንጉሣዊ ቤተሰብ ጽኑ ፍላጎቶች ላይ ነቀፋቸው እያደር ጨመረ። ይሁንና ከሐስሞናውያን ፍላጎቶች ውስጥ ሐሲዲም የተባሉትን በጣም ያሳዘናቸው የሊቀ ክህነቱን ማዕረግ እነርሱ መንጠቃቸው ነበር። ከሐሲዲም መካከል አንዳንዶቹ ከሳዶቅ ክህነት ሌላ አንቀበልም ያሉ ሲሆን በዚህም የተነሣ ሕጋዊ ባልሆነ ሹመት ከመመራት ይልቅ ላለመተባበር ራሳቸውን ከቤተ መቅደስ አምልኮ አግልለው ነበር። ከነዚህ ሰዎች ጥቂቶቹ ወደ ይሁዳ ምድረ በዳ ሄደው የኩምራንን ገዳም የመሠረቱ ሲሆን፥ የዚህን ገዳም ሥነ ሥርዓትና ውስጠ ደንብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጨው ባሕር አካባቢ ከተገኙት ጥቅልል መጻሕፍት ለመረዳት ተችሏል። እነዚህ ሰዎች በዘመኑ ከነበሩት በርካታ የባሕታውያን ቡድኖች እንደ አንዱ ሳይቆጠሩ አልቀሩም። የሳዶቅ ቤተሰብ አንድ ክፍል በግብፅ አገር ሌኦንቶፖሊስ በተባለው ሥፍራ የአይሁድ ቤተ መቅደስ እንዲሠራና በሊቀ ክህነት ማዕረግ እንዲያገለግል ተፈቅዶለት ነበር። ይሁን እንጂ ስለ አሪት ሕግ ቅንዓት የነበራቸው ሐሲዲም ከእስራኤል ውጪ የተሠራውን ቤተ መቅደስ ሊደግፉት አልፈቀዱም።

በ143 ዓክልበ የሴሌውዳውያንን መንግሥት መግዛት ይገባኛል ከሚሉት መካከል አንዱ የሆነውን ዮናታንን አጥምዶ ገድሎታል። ሆኖም አይሁድ ከሴሌውሲዳውያን ቀንበር ተላቀው ፍጹም ነፃነት እንዲጎናጸፉ ባደረገው በወንድሙ በስምዖን ተተክቷል። ይህ የአስተዳደር ነፃነት በጽሑፍ ሰፍሮ ለአይሁድ የተሰጣቸው በሴሌውሲዳውያን ንጉሥ በዳግማዊ ዲሚትሪዮስ በ142 ዓክልበ በግንቦት ወር ነበር። ከዚህም የተነሣ አይሁድ ገባሮች በመሆን ቀደም ብሎ ይከፍሉት ከነበረው የግብር ግዴታ ነጻ ሆኑ። በተጨማሪ ስምኦን በይሁዳ፥ በጌዘር ምሽግና በኢየሩሳሌም የተቀሩትን የሴሌውሲዳውያንን ወታደሮች አሸንፎ በማባረሩ አይሁዶች የተጎናፀፉትን አስተዳደራዊ ድል ፍጹም አደረገው። የሴሌውሲዳውያንም ንጉሥ የሆነው ዲሚትሪዮስ በፋርሳውያን ላይ ዘመቻ ለማካሄድ ሄዶ ስለነበር በእርሱ ላይ ለመዘመት ቢመኝም እንኳ በስምዖን ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሊወስድበት አልቻለም። ስምዖን ስላስገኘላቸው ነፃነትና ሰላም ባለውለታ ከሆነላቸው ከአይሁድ ወገኖቹ ብርቅ ሽልማቶች የተቀበለ ሲሆን በ140 ዓክልበ መስከረም ወር በታወቀው የአይሁድ ስብሰባ ላይ የስምዖንና ከእርሱ በፊት የነበሩት የወንድሞቹ የጀግንነት ድሎች ታይተው ስምዖን የሕዝቡ አስተዳዳሪ፤ የጦር ሠራዊቱ ዋና አዛዥና ወራሽ ሊቀ ካህናት እንዲሆን ታወጀ። እርሱም በተከታዩ ይህንን ሦስት ዕጥፍ የሆነውን ሥልጣን በአዲስ ኪዳን ዘመን ለምናገኛቸው ልጆቹና ተተኪዎቹ ሊያወርሳቸው ችሏል።

ስምዖን በይሁዳ ሥልጣን ለመጨበጥ ተስፋ ያደርግ በነበረው በአቡቡስ ልጅ በአማቹ በጥቶሎሚ በ135 ዓክልበ በኢያሪኮ ተገድሏል። ይሁን እንጂ የስምዖን ልጅ

ዮሐንስ ሂርካኑስ የገዳዩን ዕቅዶች በማክሸፍ አባቱን ተክቶ ሥፍራውን ከመነጠቅ አድኗል።

በስምዖን ዘመን የመጨረሻ ዓመታት ውስጥ በይሁዳ ላይ ያለው ሥልጣን እንደገና ለማጥበቅ የሞከረው የሴሌውሲዳውያን ንጉሥ አንቲዮክስ 7ኛ በዮሐንስ ሂርካኑስ ዘመን የመጀመሪያ ጥቂት ዓመታት ውስጥ በዮሐንስ ላይ ግብር ለመጫን ችሎ ነበር። ቢሆንም አንቲዮክስ 7ኛ በ129 ዓክልበ ከፋርሳውያን ጋር ባደረገው ጦርነት ውስጥ በመሞቱ የሴሌውሲዳውያን በይሁዳ ላይ የነበራቸው የበላይ ገዥነት በማያዳግም ሁኔታ አከትሟል።

አንቲዮክስ 4ኛ ይሁዳ በግዛቱ ውስጥ የነበረውን እና ለአይሁዶች የቤተ መቅደስ አስተዳደር ነፃነት የሚያዘውን የቆየ ሕገ መንግሥት ከሻረው ከ40 ዓመታት በኋላ በዮሐንስ ሂርካኑስ ዘመን በሰባተኛው ዓመት የይሁዳ መንግሥት በብርቱ ተጠናክሮአል። የሐሲዲም ጽኑ እምነት፥ የይሁዳ መቂባስ ወታደራዊ ብልሃት፥ የስምኦን የአመራር ችሎታና የሴሌውሲዳውያን መንግሥት መከፋፈል እንዲሁም መዳከም ከውጭ ሲታይ አይሁድ በአንቲዮክስ 4ኛ እጅ አጥተውት ከነበረው ነገር በላይ አስገኝቶላቸዋል። ከዚህ የተነሣ በዮሐንስ ሂርካኑስ ዘመን የተገኘው የመጀመሪያዎቹ ዓመታት ነጻነት በኋለኛው ዘመን በነበሩት ትውልዶች እንደ ወርቃማ ዘመን ቢታይ አያስደንቅም።

በአብዛኞቹ ሐሲዲምና በሐስሞናውያን ቤተሰብ መካከል የመጨረሻው መለያየት የተፈጠረው በዮሐንስ ሂርካኑስ ዘመን ነበር። የሊቀ ካህንነቱን ማዕረግ ስለተቃወሙት ተቀይሞ ዮሐንስ ከእነርሱ ጋር ተጣልቶ ነበር። እነርሱም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የፈሪሳውያን ቡድን በመሆን በታሪክ ውስጥ ይታያሉ። ፈሪሳውያን ወይም በዕብራይስጥ «ፐሩሲያም» «ተገንጣይ» የሚለው ስም ሊሰጣቸው የቻለው የቀድሞ ኅብረት በማቋረጣቸው ይመስላል። ከዚህ ይልቅ ግን ነገሩ ግልጽ ባይሆንም እንኳ ይህ ስም የተሰጣቸው ለመንጻትና ለአሥራት ሕግጋት በነበራቸው ጠንቃቃ አመለካከት የተነሳ፥ ይህንን ሐሳብ ከማይካፈሉት ጋር ያላቸውን ኅብረት በማቆማቸው ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ አሁን ፈሪሳውያን የተባሉት ሰዎች ለ50 ዓመታት ያህል ዮሐንስንና ተከታዮቹን በመቃወም ኖረዋል። እነ ዮሐንስን ይደግፉና የብሔራዊውም ሸንጎ አባላት የነበሩ የኃይማኖት መሪዎች ሰዱቃውያን በሚል መጠሪያ ከፈሪሳውያን ጋር በአንድ ዘመን ብቅ ያሉ ሲሆን በአዲስ ኪዳንም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን የሊቀ ክህነት ማዕረግ የያዙት ሀብታም ቤተሰቦች የሰዱቃውያን ወገን ነበሩ።

ዮሐንስ ሂርካኑስ ሥልጣኑን ለማራዘም በሴሌውሲዳውያን መንግሥት መዳከም ተጠቅሟል። ዮሐንስ የአይሁድን ነፃነት ካጸና በኋላ ቀደም ብሎ ከወሰዳቸው እርምጃዎች መካከል አንዱ የሰማሪያን ግዛቶች መውረርና ሰማርያን መክበብ ነበር። ይህም አንድ ዓመት የፈጀ ሲሆን በመጨረሻ ላይ ከተማይቱ ተጠቅታ ተደምስሳለች። በተጨማሪም ዮሐንስ ሴኬምን በመያዝ በፋርስ ዘመነ መንግሥት ማክተሚያ ላይ በገሪዛን ተራራ ላይ ተሠርቶ የነበረውን እና አይሁድ እጅግ የጠሉትን ቤተ መቅደስ አውድሟል። ሰማሪያውያን በሴሌውሲዳውያን ንጉሥ ፊት ቀርበው እርዳታ ጠይቀዋል፤ ይሁን እንጂ እርሱ በነገሩ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ ሮማውያን አስጠንቅቀውት ነበር። ሐስሞናውያን ማለት እነ ዮሐንስ በትግላቸው ወቅት በመጀመሪያ አካባቢ ከሮማውያን ጋር ኅብረት የመፍጠር ውል ተዋውለዋል፤ ከዚህም የተነሣ ሮማውያን ሴሌውሲዳውያንን የማዳከምና የማጥላላት ዕድል ስለፈለጉ የቀድሞውን ውል በዮሐንስ አማካይነት አድሰውታል።

ዮሐንስ በግዛቱ በስተደቡብ የሚገኙትን ኢዱማውያን ወግቶ ድል በማድረግ ግዝረትንና የአይሁድን ሃይማኖት እንዲቀበሉ አስገድዷቸዋል። በዮሐንስ ዘመን ኢዱማውያን ተብለው ይጠሩ የነበሩት ሰዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ኤዶማውያን በመባል ይታወቁ ነበር። በተጨማሪም በዮርዳኖስም አካባቢ ይገኙ የነበሩትን የግሪክ ከተሞች በቁጥጥሩ ሥር ካደረገ በኋላ ገሊላን ለመውረር ችሎ ነበር።

በገሊላ የነበረው ሥራ ከ104-103 ዓክልበ በመራው ልጁና የእርሱም ምትክ በነበረው በአርቶቡለስ የቀጠለ ቢሆንም፤ እርሱም አባቱ በኢዱማውያን ላይ እንዳደረገው በሥሩ የነበሩት ገሊላውያን የአይሁድን እምነት እንዲቀበሉ አስገድዷቸውል።

የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ ጆሲፈስ ባስፈረው መሠረት አሪስቶቡለስ አያቱና ከላይ እንደተጠቀሰው አባቱም ጭምር ረክተውበት በነበረው አስተዳዳሪ በሚለው ማዕረግ ሳይደሰት «ንጉሥ» የሚለውን ማዕረግ ለራሱ ሰጥቷል። እንዲሁም ለመንግሥታዊ ግዛቱ ምልክት እንዲሆን ዘውድ የሚመስል ነገር ጭኖ ነበር። በዚህ አኳኋን በአሕዛብ ጎረቤቶቹ መካከል ከፍተኛ ክብር እንደሚያገኝ ተስፋ ማድረጉ ጥርጥር የሌለው ቢሆንም ያወጣቸው ሳንቲሞቹ ግን የታተሙት አይሁድን በማያስቀይም የይሁዳ ሊቀ ካህን በሚለው ስም ነበር።

አርስቶቡለስ አንድ ዓመት ከነገሠ በኋላ ሲሞት ከ103 - 76 ዓክልበ ይመራ በነበረው በወንድሙ በእስክንድር ጃኒየስ ተተክቷል። እርሱም የሙት ወንድሙን ሚስት ሰሎሜ እስክንድራን አግብቷል።

ከጃኒየስ የባሰ በጣም መጥፎ ሊቀ ካህናት ሊኖር ይችላል ብሎ መገመት ያስቸግራል። ከፍተኛ በዓል ባለበት ወቅት በሹመቱ መሠረት የቤተ መቅደስ ሥነ ሥርዓት ይፈጸም ነበር፤ ይህንንም ያደርግ የነበረው ሆነ ብሎ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ የነበራቸውን የብዙዎቹን ተገዢዎቹን በተለይም የፈሪሳውያንን ስሜት ለመጉዳት አስቦ ነበር። ይህም የእርሱ አመራር ጽኑ ፍላጎት ግን ወታደራዊ ድል ለመቀዳጀት እንደ ነበር አሳይቷል። ይህንን የአመራር ስልት መከተሉ ብዙ ቅልበሳዎች አስከትሎበታል። ይሁን እንጂ በአመራር ዘመኑ መጨረሻ ላይ በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ መልካም በነበሩት ዘመናት ወቅት የእስራኤላውያን የነበረውን ግዛት በተግባር በቁጥጥሩ ሥር አድርጓል፤ ነገር ግን ይህን ሲያደርግ የሕዝቡን መንፈሳዊ ቅርስ በጣም ጎድቶ ነበር።

በሜዲትራኒያን ባሕር ዳርና በዮርዳኖስ አካባቢ የነበሩት የግሪክ ከተሞች የተለያዩ የውጊያ ዒላማዎቹ ነበሩ። ምሕረት በሌለው አቋሙ በመጠቀምና ለግሪክ ሥልጣኔ መልካም ውጤቶች ምንም ደንታ የለሽ መሆኑን በማሳየት እነዚህን አገሮች አንድ በአንድ እየከበበ ድል አድርጓቸዋል። የአኗኗሩንም ዘዬ መናኛ በሆነው የምዕራብ እስያ፥ የግሪክ ሥልጣኔና ንጉሣዊ የኑሮ ሁኔታ ቀይሶት ነበር። አይሁዳዊ ተገዢዎቹ በእርሱ ላይ ያላቸው ጥላቻ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ ነበር። ስለዚህ እርሱ በ94 ዓክልበ በዮርዳኖስ አካባቢ በናባታውያን ሠራዊት እጅ ክፉኛ ሊሸነፍ በእርሱ ላይ በማመፅ የሴሌውሲዳውያን ንጉሥ ዲሚትሪዮስን እንዲያግዛቸው ለምነውታል። ሌሎቹ የጃኒየስ አይሁዳዊ ተገዢዎች ግን እርሱን በጣም ቢጠሉትም እንኳ በሐስሞናውያን ቤተሰብ አንድ አባል ላይ የተካሄደውን ዓመፅ ለማሳካት ሲባል የሴሌውሲዳውያንን ንጉሥ መጠራት ስላስቀየማቸው ክፉኛ የሚጨቁናቸውን የንጉሣቸውን ዓላማ ለመደገፍ ፈቃደኛ በመሆን አመፁን ጸጥ እንዲያደርግ ረድተውታል። የሴሌውሲዳውያን ሠራዊት በሙሉ እንዲመለስ አድርገዋል። ጃኒየስ ጥቂት ከፍተኛ ፈሪሳውያንን ጨምሮ በአመጹ መሪዎች ላይ የወሰደው የበቀል እርምጃ በጭካኔነቱ ለብዙ ዘመን ሲታወስ ኖሯል።

ጃኒየስ መንግሥቱን ለሚስቱ ለሰሎሜ እስክንድራ በማውረሱ ንግሥት ሆና በመምራት 9 ዓመታት እንድትገዛ አስችሏታል። ሊቀ ክህነቱንም ለታላቅ ልጇ ለዳግማዊ ሂርካኑስ የሰጠችው ሲሆን፥ በአንድ ዋና አቅጣጫ ከእርሷ በፊት የነበሩትን መሪዎች የአመራር ስልት ቀይራለች፤ ይኸውም ከፈሪሳውያን ጋር በመወዳጀት በአመራር ዘመኗ ውስጥ ሁሉ የእነርሱን ምክር ታደምጥ ነበር። በ67 ዓ.ም. የእርሷ መሞት በይሁዳ ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣን የመያዝ ፍላጎት በነበራቸው በሁለት ልጆችዋ በዳግማዊ ሂርካኑስና በዳግማዊ አርስቶቡለስ እንዲሁም በተከታዮቻቸው መካከል እርስ በርስ ውጊያ አስከትሏል። ዳግማዊ አርስቶቡለስ ምኞቱ ትልቅና ተንኳሽ የነበረ ደምበኛ ሐስሞናዊ ነበር። ዳግማዊ ሂርካኑስ ግን እዚህ ግባ የማይባልና ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ሐሳቡን በደገፉለት ሰዎች በተለይም ከመካከላቸው ተሰሚነት በነበረውና አባቱ በዳኒየስ ሥር ሆኖ የኢዱሙ አስተዳዳሪ በነበረው በኢዱማዊው በአንቲፓተር በቀላሉ የተለወጠ ሰው ነበር።

በሁለቱ ወንድማማችና በደጋፊዎቻቸው መካከል የነበረው የእርስ በርስ ግጭት በ63 ዓክልበ በሮማውያን አማካይነት ቆሟል። በዚህም ይሁዳ በሐስሞናውያን አማካይነት አግኝታው የነበረው አጭር የነፃነት ዘመን አከትሟል።

በ66 ዓክልበ የሮማውያን ምክር ቤትና ሕዝብ 20 ዓመታት ለፈጀው ከፓንተስ ንጉሥ ከሚትሪዳትስ ጋር ለነበረው ጦርነት የተሳካ ፍጻሜ ለማበጀት ይችሉ ዘንድ በዚያ ዘመን እጅግ በጣም ብልህ የነበረውን የጦር መሪ ፖምፔይን ላኩት። ሚትሪዳትስ በምዕራብ እስያ ከወደቀው የሴሌውሲዳውያን ግዛትና ከጎረቤት መንግሥታት መሬት ቆርሶ በመውሰድ የራሱን ግዛት መሥርቶ ነበር። ሚትሪዳትስ ክሪሚ ወደ ተባለው ሥፍራ ሸሽቶ ራሱን በመግደሉ ፖምፔይ የሚትሪዳትስን ግዛት ለማሸነፍ ጊዜ አልወሰደበትም። ፖምፔይ ይህንን ድርጊት ከፈጸመ በኋላ ለምዕራብ እስያ አስተዳደራዊ ኑሮ መብት መስጠት እንደሚያስፈልግ ተገነዘበ። ሶርያም የሮም ክፍለ ሀገር እንድትሆን በ64 ዓክልበ የቀላቀላት ሲሆን በተጨማሪም በአይሁድ መንግሥት ውስጥ ያሉት የተለያዩ ቡድኖች በግል ጉዳዮቻቸው ውስጥ ጣልቃ እንዲገባና በጃኒየስ ልጆች መካከል የነበረውንም የእርስ በርስ ጦርነት ደግሞ እንዲያቆም ጋበዙት።

አንቲፓተርሞ ሁኔታውን የመመርመር ጥበብ ስለነበረው የሂርካኑስ ተከታዮች ከሮም ጋር እንዲተባበሩ ፈቃደኝነቱን ገልጿል። ኢየሩሳሌምም በ63 ዓክልበ በፀደይ ወራት በሮችዋን ለፖምፔይ ከፈተችለት። ይሁን እንጂ ተለይቶ ለብቻው ተገንብቶና በአርስቶቡለስ ደጋፊዎች ተይዞ የነበረው ቤተ መቅደስ በፖምፔይ ሠራዊቶች ከመወሰዱ በፊት ለሦስት ወራት የቆየ ከበባ ተደርጎበታል።

በመጨረሻም ይሁዳ አሁን የሮም ገባር ሆነች፤ ሐስሞናውያን ነገሥታት ድል አድርገው ከራሳቸው ግዛት ጋር የቀላቀሏቸውን የግሪክ ከተሞች ተነጠቀች። ሰማርያውያንም ከአይሁድ ቁጥጥር ሥር ነፃ ሆኑ። ሂርካኑስ ሊቀ ክህነቱና የሕዝብ መሪነቱ ቢጸናለትም ቅሉ ሮማውያን እርሱን እንደ ንጉሥ አንቀበለውም ስላሉ አስተዳዳሪ በሚለው ማዕረግ ረክቶ መቀመጥ የግድ ሆነበት። አንቲፓተር ይህንን የሁኔታዎች አዲስ ገጽታ ለራሱ ጥቅም ለማዋል በማሰብ ሂርከትስን መርዳቱን ቀጠለ። እነዚህ ነገሮች ከይሁዳ ጥቅም ጋር የተሳሰሩ ነበሩ።

አሪስቶቡለስና ቤተሰቡ በሮም ላይ ዓመፅ አስነሥተው በይሁዳ ራሳቸው ሥልጣን ሊጨብጡ በየጊዜው ጥረት አድርገዋል። ሆኖም ለብዙ ዓመታት ይህ ሙከራ ሊከሽፍ ችሏል። እነዚህ የይሁዳ ክፍለ ሀገሮች ይገኙ የነበረው በሮም ግዛት በስተምሥራቅ ድንበር ላይ ስለነበርና ከነርሱም ማዶ የባላንጣቸው የፓርቲያ ግዛት ይገኝ ስለነበር ተከታታይ

የሆኑት የሮም ገዢዎች በይሁዳና በሶሪያ ላይ አስተዳደራቸው ጥብቅ ነበር። የዚህ አካባቢን የጦርነት ቀልፍ ሥፍራ መሆን ለማየት በነዚህ ዓመታት የይሁዳ ታሪክ ውስጥና ድርሻቸውን ባበረከቱ በሮማውያን ታሪክ ውስጥና ብርቱ ባለሥልጣኖች በነበሩት ሰዎች ብዛት መለካት ይቻላል። ለምሳሌ ፖምፔይ ይህንን አካባቢ ከሮም ግዛት ጋር ቀላቅሎታል፤ ክራስስ ከ53 - 54 ዓክልበ የሶሪያ ገዢ በመሆን ከፓርዚያውያን ጋር ለነበረበት ውጊያ የገንዘብ ምንጭ ለማግኘት ሲል የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስና በተጨማሪም ብዙ የሶሪያውያንን መቅደሶች ዘርፏል፤ ሆኖም በ53 ዓክልበ ካርሔ በተባለው ሥፍራ በፓርዚያውያን ተሸንፎ ተገድሏል። ጁሊየስ ቄሣር በተሳሊ ውስጥ ፋርሳለስ በተባለው ሥፍራ በ48 ዓክልበ ፖምፒይን አሸንፎ የሮማውያን ዓለም ጌታ ሆኗል። የቄሣርን ገዳዮችና ተከታዮቻቸውን ፊልጵስዩስ በተባለው ሥፍራ በ42 ዓክልበ አክታቪያን ከተባለው ሰው ጋር በመሆን ድል አድርጓል። ከዚያም በኋላ የሮምን ግዛት ምሥራቃዊ ክፍለ ሀገሮች የገዛውን አንቶን በ31 ዓክልበ አክቲዮም በተባለው ሥፍራ እንዲሁም በግብፅ የነብረው የፕቶሌማውያን ንጉሣዊ ዘር የመጨረሻ መሪ የሆነችውን ክሌኦፓትራን አሸንፎ ከ27 ዓክልበ ጀምሮ የሮማውያንን ግዛት አውግስጦስ ቄሣር በመባል ብቻውን የመራው አክታቪያን ነበር። ተለዋዋጭ በነበረው የሮማውያን የርስ በርስ ውጊያ ውስጥ ሁሉ አንቲፓተርና ቤተሰቡ ማንም ይሁዳ እንዲሁም በሮማውያን ግዛት የየትኛውም ቡድን አባል ይሁን ብቻ የሮምን ሥልጣን በምሥራቅ የሚወክል ማንኛውም ዋና ተወካይ ሲመጣ ይህንን ሰው መደገፍ ቋሚ መመሪያቸው ነበር። በተለይም ጁሊየስ ቄሣር በ48 -47 ዓክልበ ባለው ወቅት የክረምት ወራት በእስክንድርያ ተከቦ በነበረበት ጊዜ አንቲፓተር ላደረገለት ድጋፍ ውለታ ነበረበት። ይህም ቢሆን ጁሊየስ ቄሣር ልዩ መብቶችን የሰጠው ለአንቲፓተር ብቻ ሳይሆን ለአይሁድ ሁሉ ነበር።

ሮማውያን በአንቲፓተር ቤተሰብ ላይ ይጥሉት የነበረው ታማኝነት ፓርዚያውያን ሶሪያንና ከነዓንን በወረሩበት ወቅት እንዲሁም በሕይወት የነበረው የዳግማዊ አሪስቶቡለስ ልጅ አንቲጎነስ የሐስሞናውይያንን ዙፋን አስመልሶ የአይሁድ ንጉሥና ሊቀ ካህናት ለመሆን በቻለው ወቅት በ40 ዓክልበ በግልፅ ታይቷል። ዳግምዊ ሂርካኑስ ዳግመኛ ሊቀ ካህናት ሆኖ እንዳይሠራ ለማድረግም ጆሮዎቹ ተቆርጠዋል። አንቲፓተር ከሞተ ቤተሰቡን ለመፍጀት ሙከራ ተደርጓል፤ በዚህም ምክንያት አንደኛው ልጁ ፋዛል ተይዞ ተገድሏል። ሆኖም ከአንቲፓተር ልጆች መካከል እጅግ ተሰጥኦ የነበረው ሄሮዶስ ወደ ሮም ሸሽቶ አንቶኒና አክታቪያን ባቀረቡት ሐሳብ መሠረት ምክር ቤቱ የአይሁድ ዕጩ ንጉሥ አድርጎታል። ፓሪዚያውያን ወራሪዎች ከይሁዳ በወጡበት ወቅት ሐስሞናዊው አንቲጎነስ መሪነቱን እንዲጨብጥ በሶርያ የነበረው ሮማዊ የጦር አዛዥ ፈቅዶለታል። ይሁን እንጂ ሄሮድስ ደግሞ ወደ ሮም የሄደበት ምክንያት ለሮማውያን በሚመች አኳኋን «ወዳጅና ጓድ» ሆኖ ይሁዳን ለማስተዳደር ሥልጣን ለመቀበል ነበር። ከዚህም የተነሣ ለሄሮዶስ የተሰጠው ድርሻ ቀላል አልነበረም፤ በተለይም በ37 ዓክልበ ከሶስት ወር ከበባ በኋላ ኢየሩሳሌምን ለመያዝ የተሳካለት ቢሆንም ከአዲሶቹ ተገዢዎቹ አትርፎት የነበረውን ጥላቻ ግን ምንም ቢያደርግ ሊያስወግደው አልቻለም። በመጨረሻም አንቲጎነስ በሰንሰለት ታስሮ እንዲገደል ትዕዛዝ ወደሰጠው ወደ አንቶኒ ተልኳል፤ ሄሮዶስም ሐስሞናዊት የነበረችውን ንግሥት ማሪያምን በማግባት ሥልጣኑ በአይሁድ ዓይን ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ሞክሮ ነበር፤ ሆኖም ይህ ጋብቻ ከድጋፍ ይልቅ ብዙ ችግር አምጥቶበታል።

በመጀመሪያዎቹ ስድስት ዓመታት የአመራር ዘመኑ የሄሮዶስ ሥልጣን አሻሚ ነበር። አንቶኒ የሄሮዶስ ጓደኛና አጋዥ ቢሆንም እንኳ ግብፅን ትገዛ የነበረችውን ክሌዎፓትራ የቀድሞ ፐቶሌማውያን አያቶችዋ ያደርጉት እንደነበረው ይሁዳን ከግዛትዋ ጋር ለማዋሐድ በመናፈቅ በአንቶኒ ላይ የነበራትን የበላይነት እስከ መጨረሻው ልትጠቀምበት ሞክራለች። በ31 ዓክልበ አንቶኒና ክሌዎፓትራ ተገልብጠው በድል አድራጊው በኦክታቪያን የሄሮዶስ ሥልጣን ቢጸድቅም እንኳ፥ ከውጭ በኩል ከነበረው ዕረፍት በስተቀር ከቤተሰቦቹ አካባቢና ከአይሁድ ጋር ከነበረው ግንኙነት አንጻር ሰላም ከድቶት ነበር። ቢሆንም የሮምን ፍላጎቶች በማስጠበቅ ሮማውያን አስተዳዳሪዎች ሊያደርጉት ከሚችሉት በተሻለ አኳኋን ይሁዳን በብርቱ ክንድ አስተዳድሯል። ዓመፅን ያለ ርኅራኄ ፈጽሞ ጸጥ አድርጓል፤ እንዲሁም የዘመነ መንግሥቱ መታሰቢያ የሆኑ አዳዲስ ከተሞች በመመሥረት የጥንቷ ሰማሪያ በነበረችበት አካባቢ የተቀረቀረችውን ሰባስቴንና በሜዲትራኒያን ባሕር ዳር ሰው ሰራሽ ወደብ የነበራትን ቄሳርያን እንዲሁም ታላላቅ ሕንጻዎችን አስገንብቷል፤ ከነዚህም መካከል እጅግ አርአያነት የነበረው ታድሶና ሰፍቶ በኢየሩሳሌም የተሠራው ቤተ መቅደስ ነበር።

ሄሮዶስ ሲሞት መንግሥቱ በሕይወት በነበሩት ሦስት ልጆቹ መካከል ተከፋፍለዋል። አርኬላዎስ አስተዳዳሪ በመሆን እስከ 6 ዓ.ም. ድረስ ይሁዳንና ሰማሪያን ያስተዳደሩ ሲሆን አንቲፓስ እስከ 39 ዓ.ም. ድረስ አስተዳዳሪ በመሆን ገሊላንና ፔሪያን አስተዳድሯል። ፊልጶስ አስተዳዳሪ ሆኖ አባቱ በሮም ቄሣሮች ፍላጎት ጸጥ ያሰኘውን ከገሊላ ባሕር በስተ ምሥራቅና በስተሰሜን ምሥራቅ የነበረውን ግዛት ተቀብሎ እስከለተ ሞቱ እስከ 34 ዓ.ም. ድረስ መርቷል።

በወንጌል ታሪክ ውስጥ ሄሮዶስ አንቲፓስ በመባል የሚጠራውን የአባቱን የአስተዳደር ሥልት ወርሶ በገሊላ፥ በፔሪያ እንዲሁም በዙሪያው ባሉት አካባቢዎች ሁሉ ምስጋና የለሹን የሮማውያን ዓላማ የማስፋፋት ተግባሩን ቀጥሏል። ከብልሃቱ በስተቀር የአባቱን ጭካኔ እንዳለ የወረሰው አርኬላዎስ ዓመፅ እንዳያስነሣ በመፍራት በሥሩ የነበሩት ተገዢዎቹ እርሱን እንዲቀይርላቸው የሮም መንግሥትን እስከመጠየቅ ድረስ ደርሰዋል። በዚህ መሠረት አርኬላዎስ ከሥልጣኑ ወርዶ እስር ቤት ገብቶአል። አገዛዙም የሮማውያን ሦስተኛ ደረጃ ክፍለ አገር ተደርጎ በአዲሱ መልክ ተቋቁሟል። በንጉሡ ገንዘብ ቤት የሚገባው የዓመት ግብር እንዲመረመር ለማድረግ የሶርያው አስተዳዳሪ ቄሬኔዎስ በይሁዳና በሰማርያ የሕዝብ ቆጠራ አካሂዷል። ይህ ቆጠራ የገሊላው ይሁዳ እንዲነሣ አድርጓል፤ ሐዋ.5፡37። ዓመፁ የከሸፈ ቢሆንም እንኳ ለቄሣር ወይም ለማንኛውም ሌላ የአራማዊ መሪ ግብር መክፈል በእስራኤል አምላክ ላይ ማመፅ ነው ብለው ባሰቡት በቀናተኛ ቡድኖች ውስጥ ለብዙ ጊዜ ቀጥሏል። እነዚህ ቀናተኞች እስከ 66 - 73 ዓ.ም. ጦርነትና የኢየሩሳሌም መደምሰስ ድረስ ሮምን ተቃውመዋል።

ከቆጠራው በኋላ ይሁዳ ሹም ወይም ወኪል በአስተዳዳሪ መልክ ተሰጥቷታል። ይህ አስተዳዳሪ በቄሣር የተሾመ ሲሆን በሶሪያው አስተዳዳሪ የበላይ ተቆጣጣሪነት ሥር ነበር። ምን ጊዜም እንቅስቃሴ የሚያደርገው በምክር ቤቱ ሳይሆን በፈረሰኛ ትዕዛዝ ነበር። በእርሱ ትዕዛዝ ሥር ተጠባባቂ ወታደሮች እንጂ ራሱን የቻለ ሠራዊት አልነበረም። እስከ 41 ዓ.ም. ድረስ የነበሩት የቀድሞ ሮማውያን ወኪሎች የሐስሞናውያን ንጉሣዊ ቤተሰብ ካከተመለት ጊዜ አንሥቶ ለሄሮዶስና ከእርሱም በኋላ ለአርኬላዎስ ተሰጥቶ የነበረውን የእስራኤልን የሊቀ ክህነት ሹመት የመሾም መብት ነበራቸው። እነዚህ ወኪሎች የተቀደሰውን ለከፍተኛ ተጫራቾች ይሸጡት ስለነበር የዚህ ሹመት ሃይማኖታዊ ክብርም

ዝቅተኛ ሆኖ ነበር። ሊቀ ካህናቱ ከሹመት የተነሣ የአይሁድን ሸንጎ ወይም የሕዝቡን የውስጥ ጉዳዮች የሚመለከተውን የሽማግሌዎች ምክር ቤት ይመራ ነበር።

የአይሁድ ሸንጎና በይሁዳ የነበረው የሮማውያን አስተዳደር በወንጌሎች ውስጥ እንደተመዘገበው በኢየሱስ ላይ በተካሄደው ምርመራ የየግል ድርሻ ነበራቸው። የሮም መንግሥት « የአይሁድ ንጉሥ» ነኝ በማለቱ በኢየሱስ ላይ የሞት ቅጣት ፈርዶበታል። በመስቀሉ ላይ የተለጠፈው መሢሕነቱን የገለጸው ወይም ያመለከተው የክስ ጽሑፍ ከአስተዳደር አንፃር የተሰጠው ትርጉም ነበር። ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት ከመቅረቡ ቀደም ብሎ የተደረገውን ምርመራ ሊቀ ካህናቱ በሊቀመንበርነት በመራ ጊዜ «መሢሕ» መሆኑን ግልጽ እንዲያደርግ ሲጠይቀው: - ከዚህ በኋላ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቀኝ ይቀመጣል በደመናም ታጅቦ ይመጣል በማለት መልሷል። በነዚህም ቃላት አማካኝነት ከዳዊት ንጉሣዊ ውርስ አንፃር ተወስዶ ከነበረው የመሢሕነት አስተዳደራዊ ትርጉም ይልቅ በውርደትና በመከራ፥ በምድር ላይ ከተገለጸው የሰው ልጅ ተልዕኮ ጋር የተሳሰረ ነበር፤ በጎ ዓላማውም የተሳካ ፍጻሜ የሚያገኘው በእርሱ አማካኝነት እንደሆነ ከእግዚአብሔር ቅን ፍርድ አግኝቷል።

ስለ መሢሑ መምጣት የተነገሩትን ትንቢቶች በኦሪት ሕግ፥ በነቢያት መጻሕፍትና በተለያዩት ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ ያለውን ወደ ኋላ ተመልሶ በማየት ማግኘት ይቻላል። ለምሳሌ በዘዳ 18:15 ውስጥ እንደ ነቢይ፤ በዘፍ.49:10፤ በዘኁ.24:17 እና በበርካታ መዝሙሮች በተለይም በመዝ.2 እና 110 ውስጥ የሚመጣው አለቃ ወይም ገዢ፤ በኢሳ.42:1፤ 53:12 የጌታ ባሪያ፤ በዳን.7:13 ውስጥ «የሰው ልጅ» የተባለለትን ብቻ መጥቀሱ በቂ ነው። እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች በሁለቱ ኪዳኖች መካከል በነበረው ዘመን በተለያየ አኳኋን «ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን» ተብሎ በዮሐ.1:45 የተጻፈውን ትንቢተ ቃል፥ የኢየሱስን መምጣት በናፍቆት የመጠበቅ ፍላጎታችንን እንዴት ሊያሳድጉት እንደቻሉ «አዋልድና ራዕይ ነክ» በተሰኘው ጽሑፍ ውስጥ ተብራርቶ ቀርቦአል።